የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
FEDERAL NEGARIT GAZETTE
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ጥር ፩፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 14
ADDIS ABABA, 4th February 2025

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፫፭፱/፪፻፲፯ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዋጅ .....ገፅ ፲፯፯፭፱/፪፻፲፯

CONTENT

Proclamation No. 1359/2025

The National Bank of Ethiopia Proclamation .....Page 17539

አዋጅ ቁጥር ፩፫፭፱/፪፻፲፯
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት የዋጋ መረጋጋት እና ጠንካራ የፋይናንስ ሥርዓት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በፋይናንስ ዘርፉ ውስጥ በየጊዜው ከሚኖሩ ለውጦች ጋር በሚጣጣም መልኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ሥልጣን እና ተግባራት እንደገና በመወሰን የቁጥጥር አቅሙን ማጎልበት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ተጓማኒነት፡

ያንጹ ዋጋ
Unit price 3170 ብር

PROCLAMATION NO. 1359/2025
THE NATIONAL BANK OF ETHIOPIA PROCLAMATION

WHEREAS, it is necessary to maintain price stability and ensure sound financial system for the rapid economic growth of Ethiopia;

WHEREAS, it is necessary to redefine the powers and functions of the National Bank of Ethiopia to enhance its regulatory competence in line with the contemporary developments in the financial sector;

WHEREAS, it is deemed necessary to

ተጠያቂነት፣ ግልጽኝነት እና አስተዳደር ከዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር ፩፻፫፻፶፱/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/"ሥልጣን የተሰጠው መንዛሪ" ማለት ከባንክ በስተቀር በውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት ለመሠማራት ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፤

፪/ባንክ" ማለት የባንክ ሥራ ለመሥራት ከብሔራዊ ባንክ ፍቃድ የተሰጠው በግል ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ባንክ፣ የውጭ ሀገር ባንክ ተቀጥላ ወይም የውጭ ሀገር ባንክ ቅርንጫፍ ነው፤

enhance the credibility, accountability, transparency and governance of the National Bank of Ethiopia in line with international best practice;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1 **Short Title**

This Proclamation may be cited as "The National Bank of Ethiopia Proclamation No.1359/2025".

2 **Definition**

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ "authorized dealer" means any person other than a bank, which is authorized by the National Bank to engage in foreign exchange transactions;

2/"Bank" means a private or state-owned bank, a foreign bank subsidiary or a branch of a foreign bank licensed by the National Bank to undertake banking business;

፫/"ቦርድ" ማለት የብሔራዊ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤

፬/"የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በፋይናንስ ተቋም የሚቀርብ ማንኛውንም አገልግሎት የሚጠቀም፣ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሚፈልግ ሰው ነው፤

፭/"የፋይናንስ ተቋም" ማለት ባንክ፣ የመድን ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ፣ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የሐዋላ ድርጅት፣ የውጭ ሀገር ባንክ እንደራሴ ቢሮ፣ የፖስታ የሐዋላ ተቋም ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን እና ፈቃድ የሚሰጠው ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፤

፮/"የውጭ ሀገር ገንዘብ" ማለት ከኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጭ በማንኛውም ሀገር ሕጋዊ ገንዘብ የሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ብሔራዊ ባንክ ያሳወቀው ማንኛውም ገንዘብ ነው፤

፯/"የውጭ ምንዛሪ" ማለት በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው ማንኛውም የውጭ ሀገር ገንዘብ፣ በውጭ ሀገር ገንዘብ የተዘጋጁ የክፍያ ማዘዣ ቼኮች፣ የሐዋላ ሰነዶች፣ የተስፋ

3/ "Board" means the National Bank's Board of Directors;

4/ "financial service consumer" means a person who uses, has used, or is contemplating to use, any of the services provided by a financial institution as to be determined by Council of Ministers Regulation;

5/ "Financial Institution" means a bank, an insurance company, a reinsurer, a micro finance institution, a micro insurance provider, payment instrument issuer, payment system operator, a capital goods finance company, a money transfer institution, representative office of a foreign bank, a postal money transfer institution or such other similar institution as determined and licensed by the National Bank;

6/ "foreign currency" means any currency other than Ethiopian legal tender which is legal tender in any country outside Ethiopia as to which the National Bank has declared it to be acceptable for payment in Ethiopia;

7/ "foreign exchange" means any foreign currency, cheques, bills of exchange, promissory notes, drafts, securities, and other negotiable instruments, expressed

ሰነዶች፣ ድራፍቶች፣ ሰነደ ሙግሌ ንዋይ፣ እንደዚሁም ሌሎች የሚተላለፉ ሰነዶችና በውጭ ሀገር ገንዘብ የተያዙ የባንክ ሂሳቦች ወይም የሚከፈሉ ወይም በውጭ ሀገር ሂሳብ ወይም የማቻቻል አሠራር የሚደረግባቸው ንብረቶች ማለት ነው፤

in foreign currency as well as bank balances in account held in foreign currency or assets in the form of foreign account crediting or set-off arrangements, expressed or payable in foreign currencies, provided they are acceptable by the National Bank;

፰/ "መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው፤

8/ "Government" means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፱/ "ገንዘብ-አክል ንብረት" ማለት ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

9/ "liquid assets" means in relation to financial institutions include:

ሀ) ጥሬ ገንዘብ፤

a) cash;

ለ) በብሔራዊ ባንክ ያለ ተቀማጭ ገንዘብ እና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የገንዘብ-አክል ንብረት ተብለው የሚወሰኑ ንብረቶች።

b) deposits in the National Bank and other liquid-assets to be determined by the National Bank Directive;

፲/ "የማክሮ ኢኮኖሚ ጥንቃቄ ፖሊሲ" ማለት በፋይናንስ ሥርዓቱ ውስጥ ያለ አንድ የፋይናንስ ተቋምን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱን መረጋጋት ማጎልበት፣ ለግለሰው ግልጽ ዓላማ ጥንቃቄ ለማድረግ የሚረዱ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ማዋል ነው።

10/ "Macro-prudential Policy" means the use of prudential tools with the explicit objective of promoting the stability of the financial system as a whole, not necessarily of the individual institutions within it;

፲፩/ "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ከመንግሥት ገንዘብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ በጊዜው ሥልጣን ያለው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ነው፤

11/"Ministry" means the Ministry of Finance or the Ministry for the time being responsible for matters relating to finance of the government;

፲፪/"የገንዘብ ዕዳዎች" ማለት ብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት እና ለኅዳም አቀፍ የፋይናንስ ድርጅቶች ካሉበት ዕዳዎች በስተቀር በገበውር ያለው ገንዘብ እና ለብሔራዊ ባንክ የሚቀርቡ ማንኛውም የገንዘብ ጥያቄዎች ናቸው፤

፲፫/"ብሔራዊ ባንክ" ማለት የሀገሪቱ ማዕከላዊ ባንክ የሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፲፬/"የሙከራ ቁጥጥር ማዕቀፍ" ማለት አዲስ የፋይናንስ አገልግሎቶች የብሔራዊ ባንክን ይሁንታ ወይም ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት በብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር እና ክትትል ሥር ሆነው በተገደበ ጊዜ በመከራ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ነዉ፤

፲፭/ "ማባዛት"ማለት በብሔራዊ ባንክ የታተመውን ወይም የተቀረጸውን የመገበያያ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ወይም የአንድ የተለየ የገንዘብ ኀድፍ ቀለም፣ ስፋት፣ ክብደት እና ፊደሎች ወይም ምልክቶች በመጠቀም በብሔራዊ ባንክ የታተመውን ወይም የተቀረጸውን የመገበያያ ገንዘብ የትኛውም ምስል ወይም ትክክለኛ ገንዘብ እንደሆነ አጠቃላይ እይታ እንዲኖር የሚያደርግ ማንኛውም ገዘፋዊ ሀልዎት ያለው ወይም ገዘፋዊ ሀልዎት የሌለው ምስል መፍጠር ሆኖ፦

ሀ) የምስሉ መጠን፣ ወይም

ለ)ምስሉን ለመሥራት ጥቅም ላይ የዋለው

12/ "Monetary liabilities" means the currency in circulation and all financial claims to the National Bank, except the National Bank's liabilities to the Government and international financial organizations;

13/ "National Bank" means the National Bank of Ethiopia, which is the central bank of the country;

14/"regulatory sandbox" means a regulatory framework that allows for a live and time-bound testing of innovative financial services under the National Bank's control and oversight, prior to authorization or licensing by the National Bank;

15/ "reproduction" shall mean any tangible or intangible image that uses all or part of a legal tender issued or minted by the National Bank, or parts of its individual design elements such as color, dimensions, weight and use of letters or symbols, which image may resemble or give the general impression of a genuine legal tender issued or minted by the National Bank, irrespective of:

a) the size of the image; or

b) the material or technique used

ቁሳቁስ ወይም ቴክኒክ፡ ወይም

ሐ)እንደ ፊደሎች ወይም ምልክቶች የመነሰሉ የመገበያያ ገንዘቡ ንድፎች መሰወዋ ወይም መጨመር ወይም አለመጨመር ግምት ውስጥ እይገባም።

to produce it; or

c) whether or not elements of the design of the legal tender, such as the letters or symbols, have been altered or added.

፲፮/ "አልባት" ማለት የመውደቅ ዕድሳቸው ሰፊ የሆነ ወይም የወደፊ የፋይናንስ ተቋማትን በተመለከተ ገንዘብ ተቀማጭ ያደረጉ ሰዎችን ከጉዳት ለመጠበቅ ወይም በአበዳሪዎች ላይ የሚደርስን ኪሳራ ለመቀነስ እማብጎት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ የተለያዩ የአልባት ዘዴዎችን በመጠቀም በብሔራዊ ባንክ የሚከናወን ሂደት ነው፤

16/ "resolution" means a process undertaken by the National Bank to deal with likely to fail or a failed financial institution so as to protect depositors, or minimize the losses to creditors through adoption of various resolution tools as provided under relevant laws;

፲፯/"በውጭ ምንዛሪ የሚፈጸም ግብይት" ማለት፡

ሀ)ውጭ ምንዛሪ ማስተላለፍ፣ መበደር፣ ማበደር፣ ማዛወር፣ መመንዘር፣ መግዛት፣ መሸጥ፣ መቀበል፣ መክፈል ወይም ሂሳብ ውስጥ ማስገባት፣ እና

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ የውጭ ምንዛሪ ማስተላለፍን፣ መበደርን፣ ማበደርን፣ ማዛወርን፣ መመንዘርን፣ መግዛትን፣ መሸጥን፣ መቀበልን፣ መክፈልን ወይም በሒሳብ ውስጥ ገቢ ማድረግን የሚያስከትል ውል፣ ስምምነት ወይም መግባባት ነው፤

17/ "transaction in foreign exchange" means:

a) the transfer, borrowing, lending, assignment, exchange, purchase, sale, receipt, payment or crediting of foreign exchange; and

b) the conclusion of any contract, agreement or understanding, as a result of which any foreign exchange is transferred, borrowed, lent, assigned, exchanged, purchased, sold, received, paid or credited within or outside Ethiopia;

፲፰/ "ዋጋ ያለው ዕቃ" ወይም "ዋጋ ያለው ነገር" ማለት ማናቸውም የገንዘብ ዋጋ ያለው ዕቃ ነው፤ ሆኖም በጉምሩክ ታሪፍና ደንብ ላይ

18/ "valuable good" or "valuable thing" means anything of value; but shall not include foreign exchange which a passenger

ዮተመለከተውን የመንገደኛ ሻንጣና መንገደኛ ወደ ኢትዮጵያ ይዘት የሚመጣውን የውጭ ምንዛሪ አይጨምርም፤

፲፱/ "ጠቅላላ የመንግሥት የህዝር ውስጥ ገቢ" ማለት የፌደራል መንግሥት፣ የክልል እና የከተማ መስተዳድሮች የባህር ውስጥ ገቢ ድምር ነው፤

፳/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፩/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ይጨምራል።

ክፍል ሁለት

የብሔራዊ ባንክ አደረጃጀት፣ ዓላማዎችና ተግባራት

፫. ሕጋዊ አቋም

፩/ በትዕዛዝ ቁጥር ፴/፲፱፻፶፭ መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ራሱን ችሎ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደር ተቋም ሆኖ ይቀጥላል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ዓላማዎቹን ለማሳካት ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሥልጣን እና ተግባራቱን ያከናውናል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያስተላልፈው ውሳኔ ገለልተኛና ተጨባጭ ምክንያትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።

brings with him into Ethiopia or any baggage of a passenger as provided in the Customs Tariff Regulation;

19/"general government domestic revenue" means the sum of the domestic revenue of Regional States, City Administrations and the Federal Government;

20/ "person" means any natural or juridical person;

21/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

PART TWO

ORGANIZATION, OBJECTIVES AND FUNCTIONS OF THE NATIONAL BANK

3. Legal Status

1/ The National Bank of Ethiopia established by Order No. 30/1963 shall continue to exist as an autonomous institution and shall henceforth be governed by this Proclamation.

2/ The National Bank in performance of its objectives shall exercise all of its powers and functions without any interference.

3/ The decision of the National Bank, adopted pursuant to this Proclamation, shall be impartial, and based on objective reason.

፬/ ብሔራዊ ባንክ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው።

፭/ ብሔራዊ ባንክ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ኖሮት፣ በተለይም፦

ሀ) ውል የመዋዋል፣

ለ) የመክሰስና የመከሰስ፣

ሐ) የንብረት ባለቤት የመሆን፣ የማግኘት፣ የመያዝና ንብረቱን በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ የማስወገድ፣ እና

መ) ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል የሚኖረውን ሥልጣን የመጠቀም እና በዚህ አዋጅ ተገዢ ሆኖ ተግባሩን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ የማድረግ፣ ችሎታ ይኖረዋል።

፮/ ብሔራዊ ባንክ ነጻነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

ሀ) የመንግሥት የፊስካል ፖሊሲን እና የብሔራዊ ባንክን የገንዘብ እና የፋይናንስ ዘርፍ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ልውውጦችን ለማሳለጥ፣ እና

ለ) ሊከሰት የሚችል የፋይናንስ ቀውስን ለመቆጣጠር፣ሚኒስቴሩና ብሔራዊ ባንክ በተሰጣቸው የሥልጣን ክልል የሚወስዷቸውን እርምጃዎች

4/ The National Bank shall be accountable to the Prime Minister.

5/ The National Bank shall have its own juridical personality, and in particular, the capacity to:

a) enter in to contract;

b) sue and be sued;

c) own, acquire, possess and dispose its property by sale or in any other manner; and

d) exercise all the powers pertaining to a legal person and may do all things necessary to carry out its functions subject to this Proclamation.

6/ Without prejudice to its autonomy, the National Bank shall closely work with the Ministry to ensure the:

a) exchange of information necessary for the implementation of the Government's fiscal policy and the National Bank's monetary and financial sector policies; and

b) coordination of measures adopted by the Ministry and the National Bank within their respective competences to manage a possible financial crisis.

ለማቀናጀት፣ ከሚኒስቴሩ ጋር በቅርበት አብሮ ይሠራል።

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የብሔራዊ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል።

ባንኩ፡-

፩/በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን መክፈትና መዝጋት፣ እና

፪/በኢትዮጵያ ውስጥ እና በውጭ ሀገር ወኪሎችን እና አገናኝ ባንኮችን መሰየምና መሻር ይችላል።

፭.የብሔራዊ ባንክ ዓላማዎች

፩/ የብሔራዊ ባንክ ዋና ዓላማ የዋጋ መረጋጋትን ለማረጋገጥ የገንዘብ ፖሊሲን ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ ሥርዓቱን መረጋጋት እና ጤናማነት ያረጋግጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ይደግፋል።

፮. የብሔራዊ ባንክ ሥልጣንና ተግባራት

ብሔራዊ ባንክ ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

4.Head Office

The National Bank shall have its head office in Addis Ababa and may:

1/ open and close branch offices in Ethiopia; and

2/ designate and revoke the designation of agents and correspondent banks in Ethiopia and abroad.

5. Objectives of the National Bank

1/ The primary objective of the National Bank shall be to formulate and implement monetary policy to maintain price stability.

2/ Without prejudice to sub article (1) of this Article, the National Bank shall ensure the stability and soundness of the financial system.

3/ Without prejudice to sub articles (1) and (2) of this Article, the National Bank shall support the general economic growth of the country.

6.Powers and Duties of the National Bank

For the fulfillment of its objectives, the National Bank shall have the powers and duties to:

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 11

፩/ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር የዋጋ መረጋጋት ግብ የማስቀመጥ፤

፪/ የገንዘብ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎችን የመወሰን፤

፫/ የራሱን የዕዳና የክፍያ ሰነዶች የማውጣት፤

፬/ የክፍት ገበያ ሥራዎች አንድ አካል በማድረግ የራሱን የአጭር ጊዜ የዕዳ ሰነዶች የማውጣት፤

፭/የገንዘብና የብድር አቅርቦት በተፈለገው መጠን መገኘትን፡እንዲሁም ተፈጻሚነት ያላቸው የወለድ ተመኖችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመቆጣጠርና የመወሰን፤

፮/ የውጭ ምንዛሪ ተመን ፖሊሲ የመቅረጽ እና ተግባራዊ የማድረግ፤

፯/ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የማክሮ ኢኮኖሚ ጥንቃቄ ፖሊሲዎችን እና ዘዴዎችን በመቅረጽ እና ተግባራዊ በማድረግ የፋይናንስ ሥርዓቱ ለሚኖረው የመቋቋም ችሎታ፡ ለስጋት አስተዳደር እና ለፋይናንስ መረጋጋት የበኩሉን አስተዋጽኦ የማድረግ፤

፰/ ለፋይናንስ ተቋማት ፈቃድ የመስጠት፡ ሥራቸውን የመቆጣጠር እና የመከታተል፤

፱/ የፋይናንስ ተቋማትን ድርጅታዊ አስተዳደር እና የቦርድ አባላት ስብጥር የመቆጣጠር፤

1/ set price stability target in consultation with pertinent government organs;

2/determine the monetary policy instruments;

3/issue its own debt and payment instrument;

4/ issue its own short-term debt instrument as part of open market operations;

5/ regulate and determine the supply and availability of money and credit as well as the applicable interest rates and other charges;

6/formulate and implement foreign exchange rate policy;

7/formulate and implement macro-prudential policies and tools in accordance with this Proclamation and other relevant laws; to contribute to the resilience of the financial system, management of risks and the maintenance of financial stability;

8/ license, regulate and supervise financial institutions;

9/ regulate corporate governance and board composition of financial institutions;

፲/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት ለፋይናንስ ተቋማት የእልባት ባለሥልጣን ሆኖ የማገልገል፤

፲፩/ የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳቦች በሙሉ የማስተዳደርና የመምራት፤

፲፪/ ማንኛውም ባንክ የሚይዘውን የተጣራ የውጭ ምንዛሪ ልክ እና ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የሚፈጽማቸውን የውጭ ዕዳ ስምምነቶችና የዕዳውን ገደብ የመወሰን፤

፲፫/ ማናቸውንም ዓይነት ተቀማጭ ገንዘብ ከውጭ ሀገር ምንጮች የመቀበል፤

፲፬/መንግሥትን በባንክ አገልግሎት፣ በገንዘብ ውክልናና በፋይናንስ አማካሪነት የማገልገል፤

፲፭/ ሕጋዊ ገንዘብን የማተም፣የመቅረጽ፣ የማሰራጨት ወይም የማሳተም፣ የማስቀረጽና የማሰራጨት፤

፲፮/ ሕጋዊ መገበያያ ገንዘብን የማስወገድ ወይም እንዲወገድ የማድረግ፤

፲፯/ ጥሬ ገንዘብ የማውጣት እና የመያዝ ገደቦችን የመወሰን፤

፲፰/ ልዩ የመታሰቢያ ሣንቲሞችን የመቅረጽ፤

፲፱/ ባንክ፣ ስልጣን የተሰጠው መንዛሪ ወይም ማንኛውም ሰው ሊይዘው የሚችለውን ያልተቀረጸ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ገደብ የመወሰን፤

10/act as a resolution authority for a financial institution as provided in relevant laws;

11/ manage and administer all international reserves of the country;

12/ set limits on the net foreign exchange position of a bank and on the terms and the amount of external indebtedness of a financial institution;

13/accept deposits of any kind from foreign sources;

14/act as a banker, fiscal agent and financial advisor to the Government;

15 /print, mint, circulate or cause to be printed, minted and circulated legal tender;

16/dispose or cause to be disposed legal tender;

17/ set cash withdrawal and holding limits;

18/ mint special commemorative coins;

19/ set limits on gold and silver bullion and foreign exchange assets which a bank, authorized dealer or any person can hold;

፭/ እንደአስፈላጊው የክፍያ፣ የማጣራትና የማወራረድ ሥርዓቶች እና ማዕከላዊ የሰነደ ሙሳለ ንዋየች ማምጃ ቤት ባለቤት የመሆን፣ የማቋቋም፣የማንቀሳቀስ፣የማዘመን፣የማሌጅ፡ የመቆጣጠርና የመከታተል፤

፳፩/ አዲስ እና ፈጠራ የታከለባቸው የፋይናንስ አገልግሎቶችን መሞከር እና ለገቢያ ማስተዋወቅ የሚያስችል የሙከራ ቁጥጥር ማዕቀፍ የመዘርጋት እና ተግባራዊ የማድረግ፤

፳፪/ ለውጭ ምንዛሪ መንዛሪዎች ፈቃድ እና ይሁንታ የመስጠት፤

፳፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር ተልዕኮውን እና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሁለትዮሽ ወይም ባለብዙ ወገን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የመፈጸም፤

፳፬/ ኢትዮጵያ የተዋዋልቻቸውን ዓለም አቀፍ የገንዘብ፡ የባንክ ስምምነቶች እና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ስምምነቶችን በማክበር የመሥራትና ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የመወከል፤

፳፭/ የፋይናንስ ተቋም ሊከተል የሚገባውን የብይ ባህሪ የመቆጣጠር እና የመከታተል፤

፳፮/ በፋይናንስ ተቋም እና በፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ መካከል አለመግባባት ሲፈጠር አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን

20/ own, establish, operate, modernize, conduct, monitor, regulate and supervise payment, clearing and settlement systems and Central Security Depository as case may be;

21/ establish and implement a regulatory sandbox framework that will enable testing and introduction of new and innovative financial services to the market;

22/ license and authorize foreign exchange dealers;

23/ enter into bilateral or multilateral international agreements for the purpose of executing its mandate and responsibilities when it deems necessary in consultation with the concerned government organ;

24/ act in compliance with international monetary, banking agreements and other related agreements to which Ethiopia is a member and represent Ethiopia in international financial institutions;

25/ regulate and supervise the market conduct of a financial institution;

26/ provide administrative decisions when a dispute arises between a financial institution and its financial service

የመስጠት፤

፳፯/ የፋይናንስ ተቋምን አገልግሎቶች ማስታወቂያ የመቆጣጠር፤

፳፰/ የፋይናንስ አካታችነትን እና የፋይናንስ ዕውቀትን የማጎልበት እና የመቆጣጠር፤

፳፱/ የሥልጠና እና የምርምር ማዕከል አቋቁሞ ሥልጠና በመስጠት እና የምርምር ሥራዎችን በማካሔድ የፋይናንስ ዘርፉን ዕድገት የመደገፍ፤

፴/ለኢኮኖሚው ጠቃሚ የሆኑ የገንዘብ፡ የፋይናንስ፡ የቁጠባና የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲዎችን ለመተንተን፣ ለመቅረጽ እና ለመወሰን ከማንኛውም ሰው መረጃን የመሰብሰብ እንዲሁም የውጭ ክፍያ ሚዛን፣ የገንዘብ አቅርቦት፣ የዋጋ ትንበያ እና ሌሎች ስታቲስቲካዊ ጠቋሚዎችን የተመለከቱ የኢኮኖሚ ጥናቶችን በማዘጋጀት የፋይናንስ መሠረተ ልማትን ጨምሮ የፋይናንስ ሥርዓቱን ደህንነት እና ታማኝነት የማረጋገጥ፤

፴፩/ያልተቀረጸ ወርቅና ብር ግዢ እና ሽያጭን በተመለከተ በመመሪያ የመወሰን፤

፴፪/ዓላማዎቹን ለማስፈጸም ማዕከላዊ ባንኮች በተለምዶ የሚኖሯቸውን ሌሎች ሥልጣኖች መጠቀምና ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

consumer;

27/ regulate advertisement of financial services of a financial institution;

28/promote and regulate financial inclusion and financial education;

29/ establish training and research center to provide trainings and conduct research works to support the development of financial sector;

30/ collect data from any person and prepare periodic economic studies, on the balance of payments, money supply, price forecasts and other relevant statistical indicators to analyze, formulate and determine monetary, financial, saving and foreign exchange policies as are useful to the economy and ensure the safety and integrity of the financial system including financial infrastructure;

31/ determine the selling and buying of gold and silver bullion by a Directive;

32/exercise such other powers and functions to execute its objectives as central banks customarily perform.

፯. የተከለከሉ ተግባራት

፭/በዚህ አዋጅ በሌላ መልኩ ከተደነገገው በስተቀር ብሔራዊ ባንክ፡

ሀ/በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ብድር በመስጠት፣ ወይም ብድር በመግዛት፣ ብድር ውስጥ በመሳተፍ ወይም ማንኛውንም ዓይነት ዕዳ የሚያስከትል ማንኛውንም ሰነድ በመጠቀም፣ ዋስትና በመስጠትም ሆነ ተመሳሳይ ውጤት ያለው ሌላ ማንኛውንም ተግባር በመፈጸም ለማንኛውም ሦስተኛ ወገን ማንኛውንም ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣ ወይም

ለ/የንግድ ማህበራትን እነሰሪዎች መግዛት እና ማንኛውንም የፋይናንስ፣ የንግድ፣ የግብርና ወይም የኢንዱስትሪ የባለቤትነት መብት መግዛት የመሳሰሉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ማካሔድ አይችልም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ ሥልጣኑና ተግባሩን ለመፈጸም አስፈላጊ በሆኑ ሕጋዊ ተቋማት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት

7. Prohibited Activities

1/ Except as otherwise provided under this Proclamation, the National Bank may not:

a) grant any financial assistance, whether in the form of a direct or indirect loan, or by purchasing a loan, participation to a loan or the use of any instrument that results in any liabilities, guarantee, or in any other similar action to any third party; or

b) practice commercial activities, such as purchasing shares of business organizations, and the acquisition of any ownership right of a financial, commercial, agricultural, or industrial nature.

2/ Notwithstanding sub -article 1 (b) of this Article, the National Bank can invest in legal entities that are necessary for the exercise of its powers and duties.

3/ Notwithstanding sub-article 1(a) of this Article, the National Bank may provide financial support to fulfill its social

የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ይችላል።

responsibilities.

ክፍል ሦስት
ስለፋይናንስ እና ኦዲት

PART THREE
FINANCE AND AUDIT

፰. ካፒታልና የመጠባበቂያ ሂሣቦች

፩/ የብሔራዊ ባንክ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ይሆናል። የብሔራዊ ባንክ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፳ ቢሊዮን (ሃያ ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚሁ ውስጥ ዝቅተኛው የተከፈለ ካፒታል ብር ፲ ቢሊዮን (አሥር ቢሊዮን ብር) ነው።

8. Capital and Reserve

1/ The capital of the National Bank shall be totally owned by the Government. The authorized capital of the National Bank is Br. 20,000,000,000 (Twenty Billion Birr) of which the minimum paid-up capital is Br. 10,000,000,000 (Ten Billion Birr).

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የተፈቀደ ካፒታል ቦርዱ በሚወስነው መጠን እና መንገድ ሊጨምር ይችላል።

ለ) ቦርዱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ከጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሳብ በማስተላለፍ ሊጨምር ይችላል።

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article:

a) The authorized capital referred under sub-article (1) of this Article may increase by an amount and in a manner to be decided by the Board.

b) The Board may increase the minimum paid-up capital referred under sub-article (1) of this Article by transfering from the General Reserve Account.

፫/ መንግሥት የብሔራዊ ባንክ የተከፈለ ካፒታል በማናቸውም ጊዜ ሳይቀንስ እንደተጠበቀ መቆየቱን ያረጋግጣል።

3/The Government shall ensure that the paid up capital of the National Bank remains undiminished at all times.

፱/ ብሔራዊ ባንክ በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ የተጣራ ትርፍ ያገኘ እንደሆነ ትርፉ በሚከተለው ቅደም ተከተል የሚከፋፈል ይሆናል፡-

ሀ) በጸሃም ግመታ ምክንያት የተገኘ እውን ያልሆነ ትርፍ ሊከፋፈሉ በሚችሉ ትርፎች ውስጥ የሚካተት ባለመሆኑ ወደ የጸሃም ግመታ መጠባበቂያ ሂሳብ ይተላለፋል፤

ለ)በንዑስ አንቀጽ ፬ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው የተጣራ ትርፍ የብሔራዊ ባንክ ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሳብ መጠን የብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ዕዳዎችን ፭ (አምስት) በመቶ እስኪሆን ድረስ ወደ ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፤ እስከዚያ ድረስም ምንም ዓይነት የትርፍ ድርሻ ለሚኒስቴሩ አይከፈልም፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት ወደ ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሳብ የሚተላለፈው የተጣራ ትርፍ መጠን ለዚሁ የተቀመጠው ከፍተኛ ገደብ ላይ ሲደርስ ቀሪው የተጣራ ትርፍ የሂሳብ ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ወደ ሚኒስቴሩ ሂሳብ ገቢ ይሆናል፤

4/ If the National Bank has net profits by the end of a financial year, it shall be distributed in the following sequence:

a) The unrealized gains obtained as a result of revaluation may not be included in the determination of distributable profits and shall be transferred to the revaluation reserve;

b) The net profit remaining after it has been deducted pursuant to sub-article (4 (a)) of this Article, shall be transferred to the General Reserve Fund until such fund equals to 5% (five percent) of the monetary liabilities of the National Bank and no distributions shall be made to the Ministry by any means until such time;

c) Where the amount of net profit required to be transferred into the General Reserve Fund in accordance with sub-article (4 (b)) of this Article exceeds the maximum threshold set thereon, the remaining net profits shall be transferred to the account of the Ministry within six months after

the end of the financial year;

መ) የዳግም ግመታ መጠባበቂያ ሂሳብ የሌለ እንደሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፌደል ተራ (ሀ) የተመለከተው የዳግም ግመታ የመጠባበቂያ ሂሳብ ከዜሮ በታች የሆነ እንደሆነ የትርፍ ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የተጣራ እሙን ያልሆነ ኪሳራ ከተጣራ ትርፍ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፤

d) In the absence of a revaluation reserve account or in the event when the revaluation reserve account referred to under sub-article (4 (a)) of this Article is negative,the net unrealized losses shall be deducted from the net profit prior to its distribution;

ሠ) የተጣራ የብሔራዊ ባንክ ኪሣራ ከጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሳቡ ላይ ተቀናሽ ይሆናል፤ እና

e) Net losses of the National Bank shall be debited from the General Reserve Fund; and

ረ) ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም ጊዜ በደረሰበት የተጣራ ኪሳራ የተነሣ ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሳቡ ከብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ዕዳዎች ያነሰ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፌደል ተራ (ለ) ተፈጻሚ ይሆናል።

f) If at any time, as a result of net losses sustained by the National Bank, the General Reserve Fund is less than the monetary liabilities of the National Bank, sub-article (4 (b)) of this Article shall be applicable.

፭/ ብሔራዊ ባንክ የሂሳብ ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ምንም ዓይነት የትርፍ ድርሻ ለሚኒስቴሩ አይከፍልም።

5/ The National Bank, before the end of financial year, shall not pay any interim dividends to the Ministry.

፮/ መንግሥት ብሔራዊ ባንክ በማንኛውም ጊዜ ዕዳውን መክፈል በሚችልበት ደረጃ ላይ መሆኑን ያረጋግጣል። ማናቸውንም የዳግም ግመታ መጠባበቂያዎች ሳይጨምር የባንኩ አጠቃላይ ሀብት ከተከፈለ ካፒታል መጠኑ በታች ከሆነ የካፒታል ጉድለቱን በመሙላት የተከፈለ ካፒታሉን በሕግ በተቀመጠው ደረጃ

6/ The Government shall ensure that the National Bank is kept solvent at all times.Provided that; where the total equity, excluding all revaluations reserves of the Bank falls below the amount of paid-up capital, the Board shall request the Council of Ministers

ለማስተካከል ዐርዱ በሚያቀርበው ጥያቄ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚኒስቴሩ የካፒታል መዋጮ እንዲያደርግ ያደርጋል።

፯/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ ሚኒስቴሩ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የገንዘብ መጠን በተራ ገንዘብ ወይም በወቅቱ ተመን መሠረት ወዲያ የሚከፈልባቸው የዕዳ ሰነዶችን በማውጣት ገንዘቡን ለብሔራዊ ባንክ ያስተላልፋል። ይህ የገንዘብ መጠን በሂሳብ ዓመቱ የመንግሥትን በጀት ለማጽደቅ በሚዘጋጀው ወይም በተዘጋጀው ሕግ ውስጥ መካተት አለበት።

7/ Following a decision by the Council of Ministers, the Ministry shall within a period of no more than one year, transfer the necessary amount in currency or in debt instruments to the National Bank with a maturity issued at prevailing market-related interest rates; such amount shall be included in the budget law that will be or has been prepared for approval by the government for that particular fiscal year.

፱. የውጭ ኦዲት

9 External Audit

፩/ማንኛውም ከዚህ ተቃራኒ የሆነ የሕግ ድንጋጌ ቢኖርም የብሔራዊ ባንክ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎች፣ ሂሳቦችና መዝገቦች በዓለም አቀፍ የኦዲት ሥራ ደረጃዎች መሠረት በውጭ ኦዲተር መመርመር አለባቸው።

1/ Notwithstanding any law requires to the contrary,the annual financial statements, accounts and records of the National Bank shall be audited by External Auditor in accordance with International Standards on Auditing.

፪/ ዐርዱ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች እና ማዕከላዊ ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም ኦዲት የማድረግ ልምድ ያለው የውጭ ኦዲተር ይሾማል።

2/ The Board shall appoint External Auditor who has experience in International Financial Reporting Standards and auditing Central Bank or

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተሾመ የውጭ ኦዲተር የሥራ ዘመኑ ከ፭ (አምስት) ዓመት ሊበልጥ የማይችል ሆኖ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን በድጋሚ ለመሾም ብቁ ሊሆን ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ መሠረት ለ፲ (አስር) ተከታታይ ዓመታት ካለማቋረጥ የሠራ ኦዲተር የመጨረሻ ቅጥሩ ከተቋረጠበት ጊዜ አንሥቶ ፭ (አምስት) ዓመት ከማለፉ በፊት እንደገና ሊሾም አይችልም።

፭/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የውጭ ኦዲተር ስለሚሾምበት አግባብ ከፌደራል ዋና ኦዲተር ጋር መመካከር ይችላል።

፲.የሂሳብ ዓመትና የሂሳብ መግለጫዎች

፩/ የብሔራዊ ባንክ የሂሳብ ዓመት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዓመት ሰኔ ፴ ቀን ያበቃል።

፪/ የብሔራዊ ባንክ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ የሂሳብ ሚዛንና ከሂሳቦች ጋር የተያያዙ ማስታወሻዎች የሚዘጋጁት በዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች መሠረት ይሆናል።

financial institution.

3/ The term office of External Auditor appointed as per sub-article 2 of this Article may not exceed a period of 5 (five) years; and may be eligible for re-appointment for one more term in office.

4/ An auditor who continuously served for a period of 10 (ten) years pursuant to sub-article 3 of this Article, may not be re-appointed before the expiration of a period of 5 (five) years from the date of termination of its last appointment.

5/ The National Bank may consult the Federal Auditor General with regards to the appointment of an External Auditor under sub-article 2 of this Article.

10. Financial Year and Financial Statements

1/ The financial year of the National Bank shall begin on 1st July and end on 30th June of the next year.

2/ The profit and loss account, balance sheet and notes to the accounts of the National Bank shall be prepared in accordance with International Financial Reporting Standards.

፫/ የውጭ አዲተር የሚያዘጋጀው የተሟላ የአዲት ሪፖርት በብሔራዊ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ የአዲት ኮሚቴ ከተመረመረ በኋላ ቦርዱ እንዲያጸድቀው ይቀርባል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ እያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንሥቶ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በውጭ አዲተር የተረጋገጠ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫውን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል።

፭/ በአግባቡ አዲት የተደረጉ እና በውጪ አዲተር የተፈረሙ የሂሳብ መግለጫዎች እያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት በተጠናቀቀ በ፮ (ስድስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ብሔራዊ ባንክ በማያወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ ይታተማሉ።

፲፩ የውስጥ አዲት የሥራ ክፍል

፩/ ብሔራዊ ባንክ በዋና የውስጥ አዲተር የሚመራ እና በአዲት፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በቴክኖሎጅና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ብቃት ያላቸው ሰዎችን ያቀፈ የውስጥ አዲት የሥራ ክፍል ይኖረዋል።

፪/ ዋና የውስጥ አዲተር፡-

ሀ) በከፍተኛ ሙያዊ ነፃነት ሥራውን ማከናወን አለበት፤

3/ A completed audit report shall be issued by the External Auditor to be reviewed by the National Bank's Board of Directors Audit Committee and be presented for the Board's approval.

4/ The National Bank shall, within six months from the end of each financial year, submit to the House of People's Representatives its annual financial statements certified by the External Auditor.

5/ Financial statements duly audited and signed by the External Auditor shall be published in the annual report to be issued by the National Bank within 6 (six) months after the end of the financial year.

11. **Internal Audit Function**

1/ The National Bank shall have an internal audit function, composed of persons having competences in audit, accounting, finance, and information technologies and shall be headed by the Chief Internal Auditor.

2/ The Chief Internal Auditor:

a) shall perform the functions of the office with a high degree of professional independence;

ለ) በአዲት ኮሚቴ አቅራቢነት በቦርዱ ለ፩ (አምስት) ዓመታት የሚሾም ሆኖ በድጋሚ ሹመቱ ለአንድ የአገልግሎት ዘመን ሊራዘም ይችላል፤

ሐ)ከዚህ ጥፋት መፈጸሙ ከተረጋገጠ ቦርዱ በሚሰጠው ምክንያታዊ ውሳኔ ከኃላፊነቱ ይሰናበታል፤

መ) ከስልጣ ወራት አስቀድሞ ለቦርዱ ሰብሳቢ ማላወቂያ በመስጠት በፍቃዱ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፤ እና

ሠ)አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ለገዥው እንዲሁም ሥራውን በተመለከተ ደግሞ በአዲት ኮሚቴው አማካኝነት ለቦርዱ ሪፖርት የሚያደርግ ይሆናል።

፫/የብሔራዊ ባንክ የውስጥ አዲት የሥራ ክፍል ተግባራት የውስጥ አዲተሮች ኢንስቲትዩት በሚያወጣቸው ደረጃዎች መሠረት ቦርዱ በሚያጸድቀው ቻርተር ውስጥ የሚደነገጉ ይሆናል።

ክፍል አራት

ስለብሔራዊ ባንክ አስተዳደር

፲፪. የብሔራዊ ባንክ ተቋማዊ መዋቅር

b) shall be appointed for a period of 5 (five) years, which may be renewed once, by the Board upon the proposal of the Audit Committee;

c) shall be dismissed by way of a reasoned decision of the Board in the event of proven serious misconduct;

d) may resign from office subject to a three month prior notification submitted to the Chairman of the Board; and

e) reports administratively to the Governor, and functionally to the Board through the Audit Committee.

3/The National Bank's internal audit function shall have its duties established in a Charter adopted by the Board in line with the standards promulgated by the Institute of Internal Auditors.

PART FOUR

GOVERNANCE OF THE NATIONAL BANK

12.Organizational Structure of the National Bank

ብሔራዊ ባንክ፡-

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣

፪/ ገዥና ምክትል ገዥዎች፣ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣ይኖሩታል።

፲፫. የቦርዱ አባላት ስብጥር፣ ብቃት እና ሹመት

፩/ ብሔራዊ ባንክ ከሚከተሉት ፱ (ዘጠኝ) አባላት የተውጣጣ ቦርድ ይኖረዋል፡-

ሀ) የብሔራዊ ባንክ ገዥ ቋሚ የቦርድ አባል ይሆናል፤

ለ)በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሾመ አንድ ምክትል ገዥ፤

ሐ)በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ የቦርድ ሰብሳቢ እና ሌሎች ፮ (ስድስት) ሥራ አስፈጻሚ ያልሆኑ አባላት።

፪/የቦርዱ ስብጥር ሴት አባላትን ያካተተ ይሆናል።

፫/ከገዥ እና ከምክትል ገዥ ውጪ የሆነ የቦርድ አባል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ዜጋ እንደሆነ፣

ለ) መልካም ስም እንዳለው፣

National Bank shall have:

1/ Board of Directors;

2/ Governor and Vice Governors; and

3/ The necessary staff.

13. Composition, Qualification and Appointment of the Members of the Board

1/ There shall be Board of the National Bank which is composed of the following 9 (nine) members:

a) The Governor of the National Bank who shall be a permanent ex-officio member;

b) One Vice Governor appointed by the Prime Minister;

c) The Chairperson of the Board and 6 (six) other non-executive members who shall be appointed by the Prime Minister.

2/ The Board composition shall include female members.

3/ A Board member other than the Governor and the Vice Governor should demonstrate that he:

a) is an Ethiopian National;

b) has a sound reputation;

ሸ) ሐቀኛ እና ታማኝ መሆኑን፣

መ)ቢያንስ የ፲ (አስር) ዓመት የሙያ ልምድ እንዳለው፣ እና

ሠ)በባንክ ሥራ፣በኢኮኖሚክስ፣ በፋይናንስ፣ በሕግ፣ በአዲት ሥራ፣ በሂሳብ አያያዝ ወይም ከብሔራዊ ባንክ ተግባራት ጋር ግንኙነት ባላቸው ሌሎች መስኮች የትምህርት ብቃት እንዳለው ማሳየት ይኖርበታል።

c) is honest and has integrity;

d) has a minimum of 10 (ten) years of professional experience; and

e) has academic qualifications in banking, economics, finance, law, auditing, accounting, or other fields relevant to the functions of the National Bank.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከገዥ እና ከምክትል ገዥ ውጭ የሆነ የቦርድ አባል፡

ሀ) ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር የሚያደርግበት ማንኛውም የገንዘብ ተቋም ወይም የገንዘብ ተቋማትን የሚቆጣጠር ማንኛውም ሕጋዊ አካል ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ የሥራ አስፈፃሚ፣ ሠራተኛ፣ ሸሪክ ወይም ባለአክሲዮን፣ እንዲሁም

ለ)የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ መሆን አይችልም።

4/Without prejudice to sub-article (3) of this Article, a Board member other than the Governor and the Vice Governor may not be:

a) a director, chief executive officer, senior executive officer, employee, partner or shareholder of a financial institution supervised by the National Bank or of any legal entity controlling a financial institution; and

b) an employee of the National Bank.

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፬ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው አንድ የገንዘብ ተቋም በይፋዊ አስተዳደር ሥር ከመደረጉ፣ በሕግ አስገዳጅነት ንብረቱ ከመጣራቱ፣ በራሱ ፍላጎት ካልሆነ በስተቀር ፈቃዱ ከመሰረዙ፣ ወይም ውህደት ከመፈጸሙ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ አግባብነት ባለው ሕግ በተደነገገው

5/ Notwithstanding to sub-article (4 (a) of this Article,if a person has been a significant shareholder of a financial institution as defined in the relevant law, or member of the board of directors, chief executive officer, or senior executive officer of a financial institution within two years preceding the receivership, compulsory liquidation, or license

መሠረት የዚሁ የገንዘብ ተቋም ወሳኝ ባለአክሲዮን፣ ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የነበረ ከሆነ የቦርድ አባል ሆኖ ሊሾም አይችልም።

withdrawal except for a withdrawal upon a request of the licensee or a merger of such entity may not be appointed as Board member.

፲፬. የቦርድ የሥራ ዘመን፣ ክፍያ እና አበል

14. Term, Remuneration and Allowance of the Board

፩/ የቦርድ አባል የሥራ ዘመን ፮ (ስድስት) ዓመት ሆኖ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን እንደገና ለመሾም ብቁ ሊሆን ይችላል።

1/ A Board member shall hold office for a period of six (6) years and may be eligible for re-appointment for one more term in office.

፪/ ለቦርድ አባላት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያና አበል በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወሰን ሆኖ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ከሚከፈለው አማካይ የክፍያ ተመን ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

2/ The Prime Minister shall fix the amount of remuneration and allowance payable to the members of the Board at minimum consistent with the comparable average rate in the financial sector of Ethiopia for a Board of Directors.

፫/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ መሠረት የተወሰነ የቦርድ የአገልግሎት ክፍያ እና አበል የሥራ ዘመናቸው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሊቀነስ አይችልም።

3/ The remuneration and allowance fixed in accordance with sub-article 2 of this Article shall not be reduced during their term of appointment.

፲፭. የቦርድ አባላት ከኃላፊነታቸው ስለሚነሡበት ወይም በፈቃዳቸው ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ

15. Removal or Resignation of Members of the Board

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ንኡስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት የተሾመ ማንኛውም የቦርድ አባል፦

Any member of the Board appointed under Article 13 sub-article 1 (c) shall be removed from office if he:

፩/ የመልቀቂያ ጽሁፍ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቦ ጥያቄው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተቀባይነት ካገኘ፤

፪/ በአንቀፅ ፶፫ ንኡስ አንቀፅ ፫ እና ፬ የተዘረዘሩትን በሹመት ወቅት ከገምቻ ውስጥ የሚገቡ መስፈርቶች ማሟላት ካቆመ፤

፫/ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች በተረጋገጠ የአካል ወይም የአዕምሮ አክል ምክንያት ሥራውን ማከናወን ካልቻለ፤

፬/ ኪሳራ ከገጠመው፤

፭/ በአምነት ማጉደል ወንጀል የተፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ወይም በማንኛውም ወንጀል ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ በሆነ እስራት ከተቀጣ፤

፮/ በቦርድ አባልነቱ ጋር በተያያዘ በከባድ የሥነ-ምግባር ችግር ተፋተኝ ከሆነ፤ ወይም

፯/ ኃላፊነቱን በንጹት እንዳይወጣ ተጽዕኖ ሊያሳድርበት በሚችል ማንኛውም ተግባር ውስጥ ከተሳተፈ ከኃላፊነቱ ይነሣል።

፲፮. የቦርድ ሥልጣን እና ተግባራት

፩/ቦርዱ ብሔራዊ ባንክ የተሰጡትን ዓላማዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብና የፋይናንስ ፖሊሲዎችን ይቀርጻል።

1/ delivers to the Prime Minister a written resignation of his appointment, and his request for resignation is accepted by the Prime Minister;

2/no longer fulfills the requirements listed under sub-article 3 and 4 of Article 13 considered at the time of his appointment;

3/ is unable to perform his duties due to physical or mental disability certified by qualified professionals;

4/ becomes bankrupt;

5/ is convicted of a criminal offence involving dishonesty or of any criminal offence for which he has been sentenced to imprisonment for a term of six months or more;

6/ is guilty of serious misconduct in relation to his duties as a member of the Board; or

7/ becomes involved in any activity which may interfere with his independence in discharging his duties.

16. Powers and Duties of the Board

1/ The Board shall formulate monetary and financial policies necessary for the achievement of the objectives entrusted to the National Bank.

፪/ቦርዱ የብሔራዊ ባንክ ሥራ አመራርን ይቆጣጠራል እንዲሁም የብሔራዊ ባንክን የሥራ አፈጻጸም ክለማቋረጥ ይገመግማል።

2/ The Board shall conduct oversight of the management of the National Bank and keep under constant review the performance of the National Bank.

፫/የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ እና ፪ ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

3/ Without prejudice to the generality of sub-article 1 and 2 of this Article, the Board shall:

ሀ) የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን ያጸድቃል፤

a) approve Directives, policies and strategies;

ለ) የብሔራዊ ባንክን በጀት፣የበጀት አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ማዕቀፍ ያጸድቃል፤

b) approve the budget of the National Bank, budget execution and financial reporting framework;

ሐ) የብሔራዊ ባንክን የሰው ሀብት ፖሊሲ ያጸድቃል፤

c) approve the National Bank's Human Resource policy;

መ) የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞችን ክፍያ እና ጥቅማ ጥቅም ያጸድቃል፤

d) approve the remunerations and benefits of the employees' of the National Bank;

ሠ) ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚቀርቡ የብሔራዊ ባንክን ዓመታዊ ሪፖርት እና ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎች ያጸድቃል፤

e) approves the annual report and annual financial statements of the National Bank that are to be submitted to the House of Peoples' Representatives;

ረ) የውስጥ ቁጥጥር፣ የስጋት ሥራ አመራርን፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን እና የደህንነት ሥርዓትን ለመጠበቅ ፖሊሲዎችን ያወጣል፤ እንዲሁም የእነዚህን ሥርዓቶች አሠራር በቀጣይነት ይገመግማል፤

f) adopt policies to maintain internal control,risk management, information technology and security system, and evaluate continuously the functioning of such systems;

ሰ) የብሔራዊ ባንክን የግዢ እና ንብረት

g) approve the National Bank's

የማስወገድ ማዕቀፍ ያጸድቃል፤

ሸ) የብሔራዊ ባንክን የሥነ-ምግባር ደንብ ያጸድቃል፤

ቀ) የብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ ሥራ አመራሮችን ሹመት እና ሽረት ያጸድቃል፤

በ)በኦዲት ኮሚቴው አቅራቢነት ዋና የውስጥ ኦዲተር ይሾማል፤

ተ) የብሔራዊ ባንክን የውጭ ኦዲተር ይሾማል፤ እንዲሁም ይሽራል፤ እና

ቸ)የብሔራዊ ባንክን ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን፣ የሥልጣን ውክልና እና ለሥራው የሚረዱ የቦርድ ኮሚቴዎችን ምሥረታ ያጸድቃል::

8/ ቦርዱ ከሚከተሉት ሥልጣኖች በስተቀር አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሥልጣኑን ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ የቦርድ አባላት፣ ለገዥው፣ ለምክትል ገዥ(ዎች) ወይም ለኮሚቴ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፦

ሀ) ፖሊሲ የመቅረጽ፣

ለ) የቦርዱ የቁጥጥር ሚና፣

ሐ) የስትራቴጂክ ውሳኔ አሰጣጥ፣

መ) የፋይናንስ ሪፖርቶችን የማጽደቅ፣

ሠ) የብሔራዊ ባንክን የውጭ ኦዲተር የመሾም እና የመሻር፣

procurement and property disposal framework;

h) approve National Bank's Code of Conduct;

i) approve the appointment and removal of senior management of the National Bank;

j) appoint the Chief Internal Auditor upon the proposal of the Audit Committee;

k) appoint and remove the External Auditor of the National Bank; and

l) approve the National Bank's organizational structure, decision-making processes, delegation of authority, and the establishment of Board committees to assist it in its duties.

4/ The Board may where it deems necessary delegate its power to one or more Board members, the Governor, Vice Governor(s), or a committee, except the powers related with:

a) policy formulation;

b) its oversight role;

c) strategic decision making;

d) approval of financial reports;

e) appointment and removal of External Auditor of the National

ረ)የብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ የሥራ አመራሮችን ሹመት እና ሽረት የማጽደቅ፣ እና

ሰ) መመሪያ የማውጣት።

፭/ማንኛውም የቦርዱ ሥልጣን በውክልና የተሰጠው ሰው፡-

ሀ) በውክልናው መሠረት ሥልጣኑን ይጠቀማል።

ለ) በውክልና የተሰጠውን ተግባር ወይም ሥልጣን ለሌላ ሰው በውክልና ሊሰጥ የሚችለው ቦርዱ አስቀድሞ በጽሑፍ ሲፈቅድ ብቻ ነው።

ሐ)በመደበኛነት ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ሪፖርት እንዲያደርግ በቦርዱ ሊታዘዝ ይችላል።

፮/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ማንኛውም ውክልና፡-

ሀ) ቦርዱ ማንኛውንም ሥልጣኑን እንዳይጠቀም ወይም ሌላ ማንኛውንም መመሪያ እንዳይሰጥ ተጽዕኖ ሊያሳድር ወይም ሊከለክል አይችልም።

ለ) በውክልና ለሚንቀሳቀስ ማንኛውም የተወካይ ተግባር ቦርዱ ባለበት ኃላፊነት ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።

ሐ) በቦርዱ ውስጥ የሚደረግ ማናቸውም ለውጥ ተጽዕኖ አያሳድርበትም።

Bank;

f) approval of the appointment and removal of senior management of the National Bank; and

g) the issuance of a Directive.

5/ A person to whom any power of the Board is delegated:

a) shall exercise the power in accordance with the delegation.

b) may sub-delegate the function or power only with the prior written consent of the Board.

c) may be instructed by the board to report regularly or as needed.

6/ No delegation under this Proclamation:

a) affects or prevents the exercise of any power or any further instructions by the Board.

b) affects the responsibility of the Board for the actions of any delegate acting under the delegation.

c) be affected by any change in the Board.

፯/በቦርዱ የተሰጠ ውክልና በማንኛውም ጊዜ ሊሰረዝ ይችላል።

፲፯.የኦዲት ኮሚቴ

፩/ ቦርዱ ቢያንስ ሶስት ሥራ አስፈጻሚ ያልሆኑ የቦርድ አባላትን ያካተተ የኦዲት ኮሚቴ ይኖረዋል። ቢያንስ አንድ የኦዲት ኮሚቴው አባል በኦዲት ወይም በሂሳብ አያያዝ ልምድ ሊኖረው ይገባል።

፪/የኦዲት ኮሚቴው የሚከተሉትን ይቆጣጠራል፦

ሀ)የብሔራዊ ባንክን የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሂደት፤

ለ)የውጭ ኦዲተሩን እንቅስቃሴ እና ገለልተኝነት፤

ሐ) የውጭ ኦዲተርን ሹመት እና ሽረት፤

መ) የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሉን፤

ሠ)በውስጥ እና በውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ የሚደረግ ክትትልን፤ እና የብሔራዊ ባንክን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እና የስጋት ሥራ አመራር ውጤታማነት።

፫/የኦዲት ኮሚቴው ዝርዝር ሥልጣን በቦርዱ ይወሰናል።

፬/የኦዲት ኮሚቴው ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ለቦርዱ ወቅታዊ መረጃዎችን

7/ A delegation given by the board may be revoked at any time.

17. Audit Committee

1/ The Board shall have an Audit Committee composed of at least three non- executive Board members. At least one member of the Audit Committee shall have experience in auditing or accounting.

2/ The Audit Committee shall oversee:

a) the process of financial reporting of the National Bank;

b) the activity and independence of the External Auditor;

c) the appointment and removal of an External Auditor;

d) the Internal audit function;

e) follow up of internal and external audit findings; and the efficiency of the internal control system and the risk management in the National Bank.

3/The detailed mandate of the Audit Committee shall be determined by the Board.

4/The Audit Committee shall meet at least once every three months, provide regular

ያቀርባል፤ እንዲሁም ስለ እንቅስቃሴዎቹ መደበኛ ሪፖርቶችን ያቀርባል፤ ይህም የብሔራዊ ባንክን የሥራ ሂደቶች ለማሻሻል የሚረዱ ምክረ-ሀሳቦችን ሊይዝ ይችላል።

፲፰. የቦርድ ስብሰባ

፩/የቦርዱ ስብሰባ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ሰብሳቢው በሌለበት ጊዜ በእሱ በተወከለው የቦርዱ አባል ይጠራል።

፪/ የቦርዱ ስብሰባዎች ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይካሔዳሉ፤ ሆኖም ግን የቦርድ ሰብሳቢው ወይም እሱ በሌለበት ጊዜ በእሱ የተወከለው ሰው በማንኛውም ጊዜ ወይም ጎቨርው ወይም ሶስት የቦርድ አባላት በጠየቁ ጊዜ ስብሰባ መጥራት ይችላሉ።

፫/ አምስት (፭) የቦርድ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሟላል፤ ሆኖም ግን የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም የእሱ ተወካይ እና ጎቨርው ወይም ምክትል ጎቨርው በስብሰባው ላይ ሊገኙ ይገባል።

፬/ የቦርዱ ውሳኔዎች በሙሉ በስብሰባው በተገኙት አባሎች አብላጫ ድምፅ ይወሰናሉ።በቦርዱ በድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም እሱ የወከለው ሰው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

updates to the Board, and submit regular reports on its activities, which may contain recommendations for the optimization of processes of the National Bank.

18. Meeting of the Board

1/ Meetings of the Board shall be called by the Chairperson or, in his absence, by a member of the Board delegated by him.

2/ Meetings of the Board shall be held at least once every month; provided that, the Chairperson or, in his absence, the person delegated by him, may call a meeting at any time or when the Governor or three board members so request.

3/ The presence of 5 (five) members of the Board shall constitute a quorum; provided, however, the Chairman or his delegate and the Governor or Vice Governor shall be present in the meeting.

4/ All decisions of the Board shall be made by a simple majority vote of the members present. In case of a tie, the Chairperson or his delegate shall have a casting vote.

፭/ በዘርዱ እየታየ ባለው ጉዳይ ላይ ጥቅም ያለው ማንኛውም አባል የጥቅሙን ምንነት ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣ እንዲሁም በዚህ ጉዳይ ላይ ቦርዱ በሚያደርገው ውይይት ላይ መሳተፍ አይችልም።

5/ A member who has an interest in a matter that is being considered by the Board shall disclose in writing to the board the nature of that interest and shall not participate in the deliberation of the board on that matter.

፮/ ቦርዱ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል።

6/ The Board shall have its own secretary.

፯/የቦርዱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች ቦርዱ በሚወስነው እኔኒንና በትክክል ይመዘገባሉ። ቦርዱ በለላ መልኩ ካልወሰነ በስተቀር ማንኛውም የቦርዱ ቃለ ጉባኤ በሚስጥር ይያዛል።

7/ Minutes of meetings of the Board shall be recorded accurately and in such form as the Board may determine. Unless the Board decides otherwise, minutes of the Board shall be confidential.

፰/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

8/ Without prejudice to the provision of this Article, the Board may adopt its own rules of meeting procedures.

፲፱. የገዥው እና ምክትል ገዥዎች ሹመት የሥራ ዘመን፣ ብቃት እና ክፍያ

19. Appointment,Term of Office,Qualification and Remuneration of Governor and Vice Governors

፩/ገዥው እና ምክትል ገዥዎች እያንዳንዳቸው ለ፮ (ስድስት) ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ሆነው ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን እንደገና ለመሾም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

1/The Governor and the Vice Governors shall be appointed by the Prime Minister for a term of 6 (six) years each and may be eligible for re-appointment for one more term in office.

፪/ ገዥው እና ምክትል ገዥዎች፡-

2/The Governor and the Vice Governors shall have demonstrated that they:

ሀ) የኢትዮጵያ ዜጋ መሆናቸውን፣

a) are an Ethiopian National;

ለ) መልካም ስም እንዳላቸው፣

ሐ) ሐቀኛና ታማኝ መሆናቸውን፣

መ) ቢያንስ የ፲ (አስር) ዓመት የመያ ልምድ እንዳላቸው፣ እና

ሠ)በኢኮኖሚክስ፣ በባንክ ሥራ፣ በፋይናንስ፣ በሕግ ወይም ከብሔራዊ ባንክ ተግባራት ጋር በተያያዙ ሌሎች መስኮች የትምህርት ብቃት እንዳላቸው ማሳየት አለባቸው።

b) have a sound reputation;

c) are honest and have integrity;

d) have minimum of 10 (ten) years of professional experience; and

e) have academic qualifications in economics, banking, finance, law or other fields relevant to the functions of the National Bank.

፫/ ገዥው እና ምክትል ገዥዎች፡

3/ The Governor and Vice Governors:

ሀ)ሙያዊ ጊዜያቸውን በሙሉ ለባንኩ አገልግሎት ማዋል አለባቸው።

a)shall devote the whole of their professional time to the service of the Bank.

ለ)ብሔራዊ ባንክ የሚቆጣጠረው ማንኛውም የገንዘብ ተቋም ወይም የገንዘብ ተቋማት የሚቆጣጠረ ማንኛውም ሕጋዊ አካል ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ፣ ሠራተኛ፣ ባለቤት ወይም ባለአክሲዮን መሆን አይችሉም።

b)shall not be a director, chief executive officer, senior executive officers, employee, partner or shareholder of any financial institution supervised by the National Bank, or of any legal entity controlling a financial institutions.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (ፎ) ፊደል ተራ /ለ/ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው አንድ የገንዘብ ተቋም በይፋዊ አስተዳደር ሥር ከመደረጉ፣ በሕግ አስገዳጅነት ንብረቱ ከመጣራቱ፣ በራሱ ፍላጎት ካልሆነ በስተቀር ፈቃዱ ከመሰረዙ፣ ወይም ውህደት ከመፈጸሙ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ አግባብነት ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት የዚሁ የገንዘብ ተቋም ወላኝ ባለአክሲዮን፣ ወይም

4/ Notwithstanding to sub-article (3 (b)) of this Article, if a person has been a significant shareholder of a financial institution as defined in the relevant law, or member of the board of directors, chief executive officer, or senior executive officer of a financial institution within two years preceding the official administration, compulsory liquidation, or license withdrawal except for a withdrawal upon a

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የነበረ ከሆነ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ ሆኖ ሊሾም አይችልም።

፫/ለገዥው እና ለምክትል ገዥዎች የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ በቦርዱ የሚወሰን ሆኖ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ከሚከፈለው አንጻራዊ አማካይ የክፍያ ተመን ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

፮/ በዚህ አንቀፅ ንውስ አንቀፅ ፫ መሠረት የተወሰነ ክፍያ የገዥው እና የምክትል ገዥው የሥራ ዘመን አስከማያልቅ ሊቀነስ አይችልም።

፳. የገዥ ወይም ምክትል ገዥ ከሥራ መልቀቅ ወይም መነሣት

፩/ ገዥው ወይም ምክትል ገዥው፡-

ሀ)የመልቀቂያ ጽሁፍ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቦ ጥያቄው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተቀባይነት ካገኘ፣

ለ)በአንቀጽ ፲፱ ንውስ አንቀጽ ፪ እና ፫ የተዘረዘሩ በሹመት ወቅት ከማሟት ውስጥ የሚገቡ መስፈርቶች ማሟላት ከቻሉ፣

ሐ)ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች በተረጋገጠ የአካል ወይም የአዕምሮ አነክ ምክንያት ሥራውን ማከናወን ካልቻለ፣

መ) ኪሳራ ከገጠመው፣

request of the licensee or a merger of such entity may not be appointed as Governor or Vice- Governors.

. 5/ The Board shall fix the remuneration of the Governor and Vice Governors at minimum consistent with the comparable average rate in the financial sector of Ethiopia.

6/ The allowance fixed for the Governor and Vice Governor in accordance with sub article 5 of this Article shall not be reduced during their term of appointment.

20. Resignation or Removal of Governor or Vice Governor

1/The Governor or Vice Governor shall be removed from office if he:

a) delivers to the Prime Minister a written resignation of his appointment, and his request for resignation is accepted by the Prime Minister;

b) no longer fulfills the requirements listed under sub article 2 and 3 of Article 19 considered at the time of his appointment;

c) is unable to perform his duties due to physical or mental disability certified by qualified professionals;

d) becomes bankrupt;

ሠ) በእምነት ማጉደል ወንጀል የተፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ወይም በማንኛውም ወንጀል በሰነት ወር ወይም ከዚያ በላይ በሆነ እስራት ከተቀጣ፣

ረ) ከሥራው ጋር በተያያዘ በከባድ የሥነ-ምግባር ችግር ጥፋተኛ ከሆነ፣

ሸ) ኃላፊነቱን በነፃነት እንዳይወጣ ተጽዕኖ ሊያሳድር በሚችል ማንኛውም ተግባር ውስጥ ከተሳተፈ ከኃላፊነቱ ላይ ይነሣል።

፪/ ገዥው ወይም ምክትል ገዥዎች በብሔራዊ ባንክ የተሰማሩበው ሹመት በተሸረሸ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በአማካሪነትም ሆነ በሠራተኝነት መሥራት አይችሉም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሠ እና ረ) መሠረት ገዥው ወይም ምክትል ገዥዎች ወንጀል የተፋተኝነት ውሳኔ ወይም ቅጣት ወይም በከባድ የሥነ-ምግባር ችግር ጥፋተኛ ሆነው ካልተገኙ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተጠቀሰው የማሰሳሰያ ጊዜ ውስጥ ቦርዱ በመመሪያ የሚወሰነውን ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው።

፳፩. የብሔራዊ ባንክ ገዥ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ የብሔራዊ ባንክ ገዥ የብሔራዊ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በዚህ አዋጅና አግባብነት

e) is convicted of a criminal offence involving dishonesty or of any criminal offence for which he has been sentenced to imprisonment for a term of three months or more;

f) is guilty of serious misconduct in relation to his duties;

g) becomes involved in any activity which may interfere with his independence in discharging his duties.

2/ The Governor or Vice Governors shall not work for any financial institution, neither as consultant nor as employee, within a period of one year after the termination of their assignment for the National Bank.

3/ During the cooling period stated under sub-article 2 of this Article, except in case the Governor or the Vice Governor leave office because of criminal conviction or sentence or found guilty of serious misconduct as stated under sub-article 1(e and f) of this Article, he shall be entitled to receive remuneration determined by a Directive to be issued by the Board.

21. Powers and Duties of the Governor of the National Bank

1/ The Governor of the National Bank shall

ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የብሔራዊ ባንክን አስተዳደርና ሥራዎች ይመራል፣ እንዲሁም የቦርዱን የፖሊሲ ውሳኔዎች ያስፈጽማል።

2/ገቨርው የብሔራዊ ባንክን ዕቅዶችና ዓመታዊ በጀት ከምክትል ገቨሮች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

3/ገቨርው የብሔራዊ ባንክ ዋና ተጠሪ በመሆን፣

ሀ/ብሔራዊ ባንክን ከሌሎች ሰዎች፣ ከመንግሥት፣ ከባዕድም አቀፍ የፋይናንስ ድርጅትና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ባሉት ግንኙነቶች ሁሉ ይወክላል፣

ለ/ብሔራዊ ባንክ በሚገባቸው ውሎች፣ ቦርዱ ባጸደቃቸው መመሪያዎች፣ ብሔራዊ ባንክ የሚያሳትማቸው የገንዘብ ኖቶችና የዋስትና ሰነዶች፣ ቦርዱ ባጸደቃቸው ዓመታዊ ሪፖርቶች እና የሂሳብ መግለጫዎች፣ደብዳቤ ምችና ሌሎች የብሔራዊ ባንክ ሰነዶች ላይ ብቻውን ወይም ከተፈቀደላቸው ሌሎች የባንኩ ሹማምንት ጋር በአንድነት ይፈርማል፣ እና

be the chief executive officer of the National Bank, and as such, he shall direct the administration and operations of the National Bank, and implement the policy decisions of the Board in accordance with this Proclamation and other relevant laws.

2/The Governor shall prepare in consultation with Vice Governors the plans and annual budget of the National Bank and, upon approval by the Board, implement the same.

3/The Governor shall be the principal representative of the National Bank, and in this capacity he shall:

a) represent the National Bank in its all relations with other persons, the Government, the International financial Organizations and other relevant international institutions;

b) sign individually or jointly with other authorized officers of the National Bank on contracts concluded by the National Bank, Directives approved by the Board, currency notes or securities issued by the National Bank, annual reports and financial statements approved by the Board, correspondence and other documents of the National Bank;

ሐ)ብሔራዊ ባንክ በሚከሰስበት ወይም በሚከሰስበት ማናቸውም ጉዳይ ራሱ ወይም በነገረ ፈጅ አማካኝነት የባንኩ ወኪል ይሆናል።

c) represent the National Bank, either personally or through counsel, in any legal proceeding to which the National Bank is a party.

፬/ ገዥው የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለማስፈጸም የሚረዱ ኮሚቴዎችን ማቋቋም ይችላል።

4/ The Governor may establish committees to assist him in the discharge of the powers and duties allocated to him.

፭/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ እና ንኡስ አንቀጽ ፯ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ገዥው ሥልጣኑን በከፊል ለምክትል ገዥዎች፣ ለሌሎች ሠራተኞች ወይም ኮሚቴዎች በውክልና መስጠት ይችላል። እንዲህ ባለው ሁኔታ በአንቀጽ ፲፮ ከንዑስ አንቀጽ ፫ እስከ ፯ የተደነገው እንደነገሩ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል።

5/ Subject to sub-article 6 and sub-article 7 of this Article, the Governor may delegate part of his powers and duties to the Vice Governors, other employee or committees. In such a case, the provisions of Article 16 sub-article 5 to 7 shall apply mutatis mutandis.

፮/ገዥው እና የሚመለከታቸው ምክትል ገዥዎች አባል ለሆኑበት ኮሚቴ አስቀድሞ በውክልና ካልተሰጠ በስተቀር የሚከተሉት የገዥው ተግባራት እና ሥልጣን የተመለከቱ ውሳኔዎች ከሚመለከታቸው ምክትል ገዥዎች ጋር በመመካከር የሚወሰኑ እና በውክልና ሊሰጡ የማይችሉ ናቸው፦

6/ Unless already delegated to a committee where the Governor and relevant Vice Governor are a member of, the Governor may not delegate his duties and powers regarding the following decisions, which shall be taken in consultation with the relevant Vice Governors:

ሀ)የሚከተሉትን የፋይናንስ ተቋምን የሚመለከቱ ውሳኔዎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የማሳሰፍ፡

a) the adoption of decisions pertaining to financial institution as per relevant laws for:

(ፅ)የአንድን የፋይናንስ ተቋም ፈቃድ የማጽደቅ፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ፡

i) the approval, suspension or revocation of license to a financial institution;

(ii) the approval of mergers and acquisitions involving financial institution;

(ii) የፋይናንስ ተቋማትን የሚያካትቱ ውህደቶችን እና ግዢዎችን የማጽደቅ፣

(iii) the approval for appointment, suspension and removal of a director, chief executive officer, senior executive officer, and External Auditor of a financial institution;

(iii) የአንድን የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ እና የውጭ አዲተር ሹመት፣ እገዳ እና ከኃላፊነት መነሣት የማጽደቅ፣

(iv) putting a financial institution under official administration, appointment and dismissal of an official administrator and approval of an official administrator's proposed action as per the relevant laws.

(iv) አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የፋይናንስ ተቋምን በይፋዊ አስተዳደር ሥር የማድረግ፣ ይፋዊ አስተዳዳሪ የመሾም እና የማሰናበት እንዲሁም ማንኛውም ይፋዊ አስተዳዳሪ ያቀረባቸውን የድርጊት ሀሳቦች የማጽደቅ።

b) Extending loans to a bank under Article 30 of this Proclamation.

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ መሠረት ለባንክ ብድር የመስጠት።

7/ To allow the Board to properly conduct its duties as described under Article 16 of this Proclamation, the Governor shall at least every month, and promptly in case of material developments concerning the achievements of the National Bank's objectives, report to the Board on main issues related to:

፯/ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፮ በተገለጸው መሠረት ተግባራቱን በአግባቡ እንዲያከናውን ለማስቻል ገዥው ቢያንስ በየወሩ እንዲሁም የብሔራዊ ባንክን ዓላማዎች መሰካት የሚመለከቱ ወሳኝ ለውጦች ሲከሰቱ ወዲያውኑ ከሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለቦርዱ ሪፖርት ያደርጋል፡-

a) the administration and operation of the National Bank;

ሀ) የብሔራዊ ባንክ አስተዳደርና አሠራር፤

b) the implementation of the monetary,

ለ) የገንዘብ፣ የምንዛሪ ተመን እና የፋይናንስ

ዘርፍ ፖሊሲዎች ትግበራ፣

ሐ) በአጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱ እና በተለይም የባንክ ሥርዓቱ ጤናማነት፣ እና

መ) የገንዘብ፣ የካፒታል እና የውጭ ምንዛሪ ገበያ ሁኔታ።

፳፪.የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥዎች ሥልጣንና ተግባራት

፩/የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥዎች በገዥው የተሰጣቸውን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናሉ።

፪/በተለይ ውክልና የተሰጠው ምክትል ገዥ ገዥው በሌለበት ጊዜ እሱን ወክሎ ይሠራል።

፳፫.የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ

፩/ የገንዘብ ፖሊሲ የማዘጋጀት እና በቦርዱ እንዲጸድቅ ሀላብ የማቅረብ ኃላፊነት ያለው የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ በብሔራዊ ባንክ ሥር ተቋቁሟል።

፪/ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴው የሚከተሉት ሰባት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ) የብሔራዊ ባንክ ገዥ.....ሰብሳቢ፣

ለ)የገዥው የሚሰየም የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ .....ምክትል ሰብሳቢ፣

exchange rate, and financial sector policies;

c) the soundness of the financial system in general and the banking system in particular; and

d) the state of the money, capital and foreign exchange markets.

22. Powers and Duties of the Vice Governors of the National Bank

1/The Vice Governors of the National Bank shall perform functions specifically assigned to them by the Governor.

2/The Vice Governor who is specifically delegated shall act on behalf of the Governor in his absence.

23. Monetary Policy Committee

1/ The Monetary Policy Committee is here by established under the National Bank by this Proclamation with the responsibility to prepare and propose monetary policy to be approved by the Board.

2/ The Monetary Policy Committee shall consist of the following seven members:

a) The Governor of the National Bank……chair person;

b) Vice Governor of the National Bank designated by the Governor…deputy chairperson;

ሐ)በገዥው የሚሾሙ አምስት የብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ፖሊሲ ትንተና እና አፕሬሽን ባለሙያዎች፣..... አባላት፣

c) five Monetary policy analysis operations experts of the National Bank as appointed by Governor.....members;

፫/ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴው የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ያልሆኑ እና በገዥው አቅራቢነት በቦርዱ የሚሾሙ ሁለት የሙያ ባለሙያዎችን ሊያካትት ይችላል። እነዚህ የሙያ ባለሙያዎች፦

3/ The Monetary Policy Committee may include two external experts who are not employees of the National Bank and who will be appointed by the Board up on the recommendation of the Governor; these external experts:

ሀ) በገንዘብ ፖሊሲ ሁሪያ ባላቸው ዕውቀት እና ልምድ መሠረት መመረጥ አለባቸው፤

a) shall be selected based on their knowledge and experience in Monetary policy;

ለ) ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው የገንዘብ ተቋማት ወይም የገንዘብ ተቋማትን የሚቆጣጠር ማንኛውም ሕጋዊ ተቋም ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ፣ ሰራተኛ፣ ሽርክ ወይም ባለአክሲዮን መሆን አይችሉም፤

b) shall not be a director, chief executive officer, senior executive officer, employee, partner or shareholder of a financial institution supervised by the National Bank or of any legal entity controlling a financial institution;

ሐ)የአገልግሎት ዘመናቸው ሶስት ዓመት ሆኖ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ።

c) shall serve for the term of three years and may be re-elected for additional one term.

፬/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ሠራተኞቹ ያልሆኑ የውጭ ባለሙያዎችን የሾመ እንደሆነ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ አባላት የሆኑት የገንዘብ ፖሊሲ ትንተናና አፕሬሽን ባለሙያዎች ቁጥር በዚሁ መሠረት ይቀነሳል።

4/ If the National Bank appoints external experts who are not its employees in accordance with sub-article 3 of this Article, the number of monetary policy analysis and operation experts who are members of the Monetary policy committee will be reduced accordingly.

፩/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ለሚሾሙት የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ አባላት የሚከፈላቸው የአገልግሎት ክፍያና አበል በቦርዱ ይወሰናል፡

5/ The Monetary Policy Committee members that are appointed in accordance with sub-article 3 of this Article shall be paid such remuneration and allowance as may be determined by the Board.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የተሾመ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ አባል፡-

6/ The Board may remove a member of the Monetary Policy Committee appointed in accordance with sub-article 3 of this Article if he:

ሀ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ ፊደል ተራ (ለ) ሥር የተመለከቱ እና በሹመቱ ወቅት ከግምት ውስጥ የገቡ መስፈርቶችን ማሟላት ከቻሙ፤

a) no longer fulfills the requirements listed under sub-article 3 (b) of this Article considered at the time of his appointment;

ለ) የኮሚቴው አባል እንደመሆኑ መጠን ካሉት ተግባራት ጋር በተያያዘ በክብድ የሥነ-ምግባር ችግር ጥፋተኛ ከሆነ፤

b) is guilty of serious misconduct in relation to his duties as a member of the committee;

ሐ) አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት ከከሰረ፤

c) becomes bankrupt as stipulated under the relevant laws;

መ) ኃላፊነቱን በነፃነት አንዳይወጣ ተጽዕኖ ሊያሳድር በሚችል ማንኛውም ተግባር ውስጥ ከተሳተፈ፤

d) becomes involved in any activity which may interfere with his independence in discharging his duties;

ሠ) ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች በተረጋገጠ የአካል ወይም የአዕምሮ እክል ምክንያት ሥራውን ማከናወን ካልቻለ፤

e) is unable to perform his duties due to physical or mental disability certified by qualified professionals;

ረ)በአምነት ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ከሆነ ወይም በማንኛውም ወንጀል በስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ እስራት ከተቀጣ፤

f) is convicted of a criminal offence involving dishonesty or any criminal offence for which he has been sentenced to imprisonment

ቦርዱ ከኃላፊነቱ ሊያሰናብተው ይችላል።

for six months or more;

7/ The Monetary Policy Committee:

a) shall meet as determined by a Directive to be issued by the Board and whenever necessary upon invitation by the Chairperson or in his absence, by the Deputy Chairperson.

b) shall constitute a quorum when at least five (5) of the members are present; however, one of them shall be the Governor or Vice Governor.

c) decision shall be made by simple majority vote of the members present. In case of a tie, the Chairperson or his delegate shall have a casting vote.

d) may adopt its own rules of meeting and internal working procedures without prejudice to the provisions of this Article.

8/ The Monetary Policy Committee shall have its own secretary.

9/ The National Bank shall publish a monetary policy statement when the board approves the recommendations of the Monetary Policy Committee with the rationale for such decision.

፯/ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴው፡

ሀ) በቦርድ በሚወሰን መመሪያ መሰረት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ወይም እሱ በሌለበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው በሚያስተላልፈው ጥሪ ይሰበሰባል፤

ለ) ቢያንስ አምስት አባላት (፭) በሚገኙበት ጊዜ የሰብሰባው ምልዓተ ጉባኤ ይሟላል፤ ሆኖም ከመካከላቸው አንዱ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ መሆን አለበት።

ሐ)ውሳኔ የሚወሰነው በስብሰባው በተገኙት አባሎች አብላጫ ድምፅ ይሆናል። ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወይም የወከለው ሰው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

መ) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የራሱን የስብሰባ እና የውስጥ አሠራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፰/የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴው የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል።

፱/ ቦርዱ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ ሲያጸድቅ ብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ፖሊሲ ውሳኔ መግለጫ ከነምክንያቱ ያወጣል።

ክፍል ፱. የፋይናንስ መረጋጋት ኮሚቴ

፩/ የሚከተሉት ሥልጣኖች ያሉት የፋይናንስ መረጋጋት ኮሚቴ በዚህ አዋጅ በብሔራዊ ባንክ ሥር ተቋቁሟል፡-

ሀ) በፋይናንስ ሥርዓቱ ላይ ያሉ ሥርዓታዊ ስጋቶችን በየጊዜው መገምገም፣ መተንተን እና መለየት፤

ለ) የማክሮ እና የማይክሮ ኢኮኖሚ ጥንቃቄ ፖሊሲዎችን ቦርዱ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ማቅረብ፤ እና

ሐ)ከመጨረሻ አማራጭ አበዳሪ ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን እና ሴሎች ብሔራዊ ባንክ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለማስተዳደር ሊጠቀምባቸው የሚችሉ መገልገያዎችን ቦርዱ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ማቅረብ።

፪/የፋይናንስ መረጋጋት ኮሚቴ የሚከተሉት ሰባት (፯) አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የብሔራዊ ባንክ ገዥ.....ሰብሳቢ፤

ለ)የገዥው የሚሰየም የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ .....ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ) ለተሰየሙበት ኃላፊነት ተገቢው ዕውቀት እና ልምድ ያላቸው በገዥው የሚሾሙ አምስት (፭) የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞች..... አባላት።

24. Financial Stability Committee

1/ The Financial Stability Committee is here by established under the National Bank by this Proclamation with a mandate to:

a) regularly assess, analyze and identify systemic risks to the financial system;

b) propose macro and micro prudential policies to be decided by the Board; and

c) propose policies related to the lender of last resort and other tools at the National Bank's disposal for crisis management to be decided by the Board.

2/ The Financial Stability Committee shall consist of the following seven (7) members:

a) The Governor of the National Bank……chairperson;

b) Vice Governor of the National Bank as designated by the Governor…deputy chairperson;

c) five (5) Employees of the National Bank who possess knowledge and experience relevant for the designated responsibility as appointed by the

ሸ/ የፋይናንስ መረጋጋት ኮሚቴው፦

ሀ) በየውሩ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ወይም አሉ በሌለበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው በሚተላለፍ ጥሪ ይሰበሰባል፤

ለ)ቢያንስ አምስት አባላት በሚገኙበት ጊዜ የሰብሰባው ምልዓተ ጉባኤ ይሟላል፤ ሆኖም ከመካከላቸው እንዱ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ መሆን አለበት፤

ሐ)ውሳኔ የሚወሰነው በስብሰባው በተገኙት አባላት አብላጫ ድምፅ ይሆናል። ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወይም የወከለው ሰው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

መ)የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የራሱን የስብሰባ እና የውስጥ አሠራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፬/የፋይናንስ መረጋጋት ኮሚቴው የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

፭/የፋይናንስ መረጋጋት ኮሚቴው በግጭት እንድ ጊዜ የፋይናንስ ሥርዓቴን መረጋጋት በተመለከተ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ሪፖርቱም በቦርዱ ከጸደቀ በኋላ የሚታተም ይሆናል።

Governor…Members.

3/ The Financial Stability Committee:

a) shall meet every month and whenever necessary upon invitation by the Chairperson or in his absence, by the Deputy Chairperson;

b) shall constitute a quorum when at least five of the members are present; however, one of them shall be the Governor or Vice Governor;

c) decision shall be made by simple majority vote of the members present. In case of a tie, the Chairperson or his delegate shall have a casting vote;

d) may adopt its own rules of meeting and internal working procedures without prejudice to the provisions of this Article.

4/ The Financial Stability Committee shall have its own secretary.

5/ The Financial Stability Committee shall once a year prepare a report on the stability of the financial system; such report shall be published after the approval of the Board.

፳፫. የአምነት ግዴታዎች

25. Fiduciary Obligations

፩/የቦርዱ አባላትና የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ያልሆኑ የውጭ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ አባላት ሕጋዊ ተግባሮቻቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት፡-

1/ In the course of discharging their lawful duties, members of the Board and the external members of the Monetary Policy Committee who are not employees of the National Bank, shall be obliged to:

ሀ) ለብሔራዊ ባንክ ጥቅም የመሥራት እና የብሔራዊ ባንክ ጥቅምን ከግል ጥቅማቸው የማስቀደም፣

a) act for the benefit of the National Bank and put the interests of the National Bank prior to their private interests;

ለ)የሥራ ኃላፊነታቸውን ለግል ጥቅማቸው ያለመጠቀም፣

b) take no advantage of their professional status for their personal benefit;

ሐ)የጥቅም ግጭት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ሁኔታዎች የመራቅ ግዴታ አለባቸው።

c) avoid any situations which may give rise to conflicts of interests.

፪/ ማንኛውም የቦርድ አባል እና የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ የውጭ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴ አባል፡

2/A Board member and an external Monetary Policy Committee member who are not employees of the National Bank must promptly and fully disclose to:

ሀ) በቅጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የያዘውን ወይም ከራሱ ጋር የሚገናኝ ማንኛውንም የግል፣ የንግድ፣ የገንዘብ፣ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ ወይም ሌላ ጥቅም አስከ ሁለተኛ ደረጃ ያሉ የቤተሰቡ አባላት በቅጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የያዙትን ጥቅም ጨምሮ ሙሉ በሙሉ ቦርዱ ወይም የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴው እየተወያየበት ያለበትን ጉዳይ ወዲያውኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

a) the Board any personal, commercial, financial, agricultural, industrial, or other interests that may directly or indirectly hold or be associated with, including holdings by family members up to the second degree, when such interests are under consideration by the Board or the Monetary Policy Committee. In such cases, the

እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች ምንም እንኳን የጥቅሞቹ መገለጽ አባሉን ምልዓተ ጉባኤ ውስጥ እንዳይቆጠር ባያግደውም አባሉ እንደዚህ ካሉት ጥቅሞች ጋር ግንኙነት ባላቸው ውይይቶችም ሆነ ድምጽ የመስጠት ሂደት ከመሳተፍ መቆጠብ ይኖርበታል።

ለ) እራሱ ወይም ማንኛውም እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለ የቤተሰቡ አባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የያዘውን ወይም ከራሱ ጋር የሚገናኝ የግል፣ የንግድ፣ የፋይናንስ፣ የግብርና፣ የኢንዱስትሪም ሆነ ሌላ ማንኛውም ወሳኝ ዕዳ ወይም ጥቅም እንዲሁም ማናቸውንም ተዛማጅ ለውጦች ለብሔራዊ ባንክ ሙሉ በሙሉ እና ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

ክፍል አምስት
ብሔራዊ ባንክ ከመንግሥት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

፳፮. የመንግሥት የገንዘብ አስተዳደር ተወካይና ባንክ መሆን

፩/ብሔራዊ ባንክ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት የመንግሥት ወኪልና ባንክ ሆኖ ይሠራል፣ በዚህም መሠረት በመንግሥት ስም እና ሂሳብ ለመንግሥት የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፣

member must abstain from participating in any discussions or voting related to these interests, although disclosure of such interests will not disqualify the member from constituting a quorum.

b) the National Bank any significant indebtedness or interests, whether personal, commercial, financial, agricultural, industrial, or other, that he or his family member up to the second degree may directly or indirectly hold, or be associated with, as well as any related changes.

PART FIVE
RELATIONS OF THE NATIONAL BANK WITH THE GOVERNMENT

26. Fiscal Agent and Banker for the Government

1/The National Bank shall act as a fiscal agent and banker for the Government and, in that capacity, it shall in the name and for the account of the Government, engage in the following transactions;

ሀ) ተቀማጭ ገንዘብ ይቀበላል፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያሉ የኢትዮጵያ መንግስት ተቀማጭ ገንዘቦችን ይሰበስባል፣ በአደራ ያስቀምጣል፣ ክፍያ ይፈጽማል ወይም ያስተላልፋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ስም እነዚህን ተግባራት እንዲያከናውኑ ሊወክል ይችላል፣ በሚኒስቴሩ ሲጠየቅ በዚህ አዲጓን የተደነ ሂሳቦችን በሚመለከት መረጃዎችን ያቀርባል፤	a) accept deposits, collect or take custody of funds deposited by the Government in Ethiopia or abroad, and remit or effect payments and, where necessary, assign banks to carry out these functions in its name and for its account; furnish information regarding such accounts as and when requested by the Ministry;
ለ)ቼኮችን፣ የሐዋላ ሰነዶችን፣ የተስፋ ሰነዶችንና የዋስትና ሰነዶችን ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል ወይም በአደራ ተረክቦ ያስቀምጣል፤	b) purchase, sell, transfer or take custody of cheques, bills of exchange, promissory notes and securities;
ሐ)እንደ ወርቅና ብር ያሉትን የከበሩ ማዕድናትና የውጭ ኣገር ገንዘብ ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል ወይም በአደራ ተረክቦ ያስቀምጣል፤	c) purchase, sell, transfer or take custody of precious metals such as gold and silver, and foreign exchange;
መ)በሚኒስቴሩ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በተለይ የተዘረዘሩ የመንግሥት ሂሳቦችን ያስተዳድራል፤	d)administer expressly specified Government accounts in accordance with the arrangements to be made with the Ministry;
ሠ)በሚኒስቴሩ ሥልጣን ሲሰጠው የመንግሥት ዕዳን ያስተዳድራል፣ የመንግስት የግምጃ ቤት ሰነዶችንና ቦንዶችን እንዲሁም ሌሎች የዋስትና ሰነዶችን ያወጣል፤	e)upon authorization by the Ministry, manage public debt transactions; and issue treasury bills, bonds, and other securities of the Government; and
ረ)በመንግሥት የወጡ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተላለፉ የግምጃ ቤት ሰነዶችንና ቦንዶችን በሁለተኛ ደረጃ ገበያ ይገዛል፣ ይሸጣል።	f) buy and sell on the secondary market unconditional negotiable treasury bills and government bonds issued by the

ለ/ብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት የገንዘብ አስተዳዳር ሆኖ ሲያገለግል ያወጣውን የሥራ ማስኬጃ ወጪ ሚኒስቴሩ ይመልሳል።

፳፯.ብድር

፩/ በዚህ አዋጅ በግልጽ ካልተፈቀደ በስተቀር ብሔራዊ ባንክ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለፌደራል፣ ለክልል፣ ለማንኛዉም የታችኛው የመንግሥት የአስተዳደር እርከን፣ የከተማ አስተዳደር ወይም የመንግሥት ተቋም ብድር መስጠት አይችልም።

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዋሬ ገንዘብ ፍሰት ላይ የተመሠረተ ጊዜያዊ የአበር ድራፍት አገልግሎት ከ፲፪ ወራት ላልበለጠ ጊዜ ለፌደራል መንግሥት ሊሰጥ ይችላል። አንዘህ ጊዜያዊ የአበርድራፍት አገልግሎቶች ካለፉት ሶስት የበጀት ዓመታት አማካይ ዓመታዊ ጠቅላላ የመንግሥት የሀገር ውስጥ ገቢ ከ፲፭ በመቶ (አሥራ አምስት በመቶ) መብለጥ የለባቸውም።

፫/ ለመንግሥት የተሰጠ ጊዜያዊ አበር ድራፍት የመክፈያ ጊዜው ሲደርስ ሲከፈል ይገባል አንጂ አይተላለፍም። ማንኛውም አንደዚህ ዓይነት ጊዜያዊ አበር ድራፍት በገንዘብ ፖሊሲ ተመን ላይ ተመሥርቶ የሚሰላ የወለድ ተመን ይታሰብበታል።

Government.

2/The Ministry shall reimburse the cost incurred by the National Bank acting as a Banker for the Government.

27. Credit

1/The National Bank shall not extend direct or indirect credit to the Federal, Regional, Local Government, City Administration or Public Institution unless explicitly allowed by this Proclamation.

2/The National Bank may provide temporary overdrafts on a Cash Flow Facility for the Government for duration no longer than 12 months. These temporary overdraft facilities shall not exceed 15 % (fifteen percent) of average annual general government domestic revenue of the previous three fiscal years.

3/ A temporary overdraft made to the Government shall be repaid upon its maturation and shall not be rolled-over. Any such temporary overdraft facilities shall bear interest rate calculated at monetary policy rate as determined by the National Bank.

፬/ብሔራዊ ባንክ በቀጣይ የሂሳብ ዓመት ተጨማሪ ኦቨር ድራፍት ለመስጠት የሚችለው ያልተከፈለው የኦቨር ድራፍት መጠን በተቀመጠለት የመክፈያ ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው።

4/ The power of the National Bank to make further overdrafts in a subsequent financial year shall not be exercised unless the amounts due in respect of the outstanding have been repaid in full within the maturity period.

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ እና ፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ መንግሥት በዚህ አንቀጽ ከተመለከተው ገደብ በላይ የሆነ ብድር ከብሔራዊ ባንክ ሊጠይቅ ይችላል። በዚህ መልኩ የሚሰጥ ማንኛውም ተጨማሪ ብድር የብሔራዊ ባንክ የዋጋ መረጋጋትን የማረጋገጥ ዓላማ ሳይጣረስ፣ የፌደራል መንግሥትን የመንግሥት ብድር ጣሪያ ባከበረ መልኩ፣ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት በጊዜ የተገደበ እና በገበያ ተመን ወለድ የሚታሰብበት ይሆናል።

5/ Without prejudice to sub-article 2 and 4 of this Article, in the event of a force majeure the Government may request the National Bank for any advance or loan beyond the limit provided under this Article. Any such additional advance or loan shall be without prejudice to the National Bank's objective of ensuring price stability, comply with the Federal Government's limits on public debt, be limited in time as determined by the National Bank and remunerated at a market interest rate.

፮/ ለዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ፭ አፈጻጸም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ማለት ያልተጠበቀ የማህበረሰብ ጤና እክል፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ ድርቅ ወይም አግባብነት ያለውን ሕግ መሠረት አድርጎ የታወጀ አጠቃላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወይም በፌደራል መንግሥት ገቢ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉልህ የውጭ የኢኮኖሚ ለውጦች ማለት ነው።

6/ For the purposes of sub- -article 5 of this Article force majeure means an unexpected public health crisis, natural disaster, drought, or a general state of emergency as promulgated by relevant law or significant external economic developments that negatively impact the Federal Government's revenue.

፮/ ብሔራዊ ባንክ ለማንኛውም ብድር፣ ቅድመ ክፍያ ወይም ኢንቨስትመንት ዋስትና አይሰጥም።

፰/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውንም የግምጃ ቤት ሰነድ፣ ቦንድ እና ሌሎች የመንግሥት ዋስትናዎችን በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ አይገዛም።

ክፍል ስድስት

ብሔራዊ ባንክ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

፳፰. ፈቃድ መስጠት፣ መቆጣጠር፣ መከታተል እና እልባት

፩/ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ ተቋማትን እና የፋይናንስ ሥርዓቱን መረጋጋትና ጤናማነት ለማስጠበቅ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ለየብቻ እና እንደሁኔታው በጋራ ለፋይናንስ ተቋማት ፍቃድ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል እንዲሁም ክትትል ያደርጋል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ለፋይናንስ ተቋማት የእልባት ባለሥልጣን ሆኖ ይሠራል። በዚህም መሠረት በፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ የሚፈጠርን መስተጓጎል በማስወገድ፣ የወደቀ የፋይናንስ ተቋምን ወላጃ ተግባራት በማስተባበል

7/ The National Bank shall not guarantee any loan, advance or investment.

8/ The National Bank shall not purchase any treasury bills, bond, and other government securities on the primary market.

PART SIX

RELATIONS OF THE NATIONAL BANK WITH FINANCIAL INSTITUTIONS

28. Licensing, Regulation, Supervision, and Resolution

1/ The National Bank shall license, regulate and supervise financial institutions, on an individual basis and as the case may be, on a consolidated basis in accordance with this Proclamation and other relevant laws, in order to promote the stability and soundness of financial institutions and the financial system.

2/ The National Bank shall act as the resolution authority of financial institutions. In that capacity, it shall prepare the financial institution for the resolution and take actions against a failed one as prescribed in

እና የእልባት ተግባር በሕዝቡ ላይ የሚያስከትላቸውን ወጪዎች በመቀነስ የፋይናንስ ሥርዓቱን መረጋጋት ለማስጠበቅ አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት የፋይናንስ ተቋማትን ለእልባት ያዘጋጃል እንዲሁም የወደቀ የፋይናንስ ተቋም ላይ እርምጃዎችን ይወስዳል።

፳፱. የገንዘብ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች

፩/ብሔራዊ ባንክ የዋጋ እና የውጪ ምንዛሪ ተመን መረጋጋትን ለማስጠበቅ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡-

ሀ) ዕዳቸውን መክፈል ከሚችሉ እና በብሔራዊ ባንክ የሚወሰነውን በቂ ዋስትና ማቅረብ ከሚችሉ ባንኮች ጋር ብድር መፈጸም፤

ለ)የፋይናንስ ሰነዶችን፣ የውጭ አገር ገንዘብ ወይም የከበሩ ማዕድናትን በቀጥታ መግዛት እና መሸጥ ወይም መልሶ ለመግዛት ወይም ለማበደር ግዴታ መግባት፤ እና

ሐ) በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ የዕዳ ሰነዶችን ማውጣት።

፪/ብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ፖሊሲ ሥራዎቹ አንድ አካል በማድረግ ብቁ ለሆነ ባንክ ስታንዲንግ ፋሲሊቲዎችን በተቀማጭ፣ በማግስቱ በሚመለስ ብድር እና በዕለቱ

accordance with pertinent laws, in order to maintain the stability of financial system by avoiding a disruption in the financial system, preserving the continuity of critical functions of a failed financial institution and minimizing the costs of resolution to the public.

29. Monetary Policy Instruments

1/The National Bank may for the purpose of maintaining price and exchange rate stability, conduct the following operations:

a) credit transactions with banks provided that they are solvent and could provide adequate collateral as determined by the National Bank;

b) the direct purchase and sale or with a commitment to repurchase or lend financial instruments,

foreign currencies or precious metals; and

c) issue debt securities with a short-term maturity.

2/ As part of its monetary policy operations, the National Bank may offer to an eligible bank, access to standing facilities in the form of a

በሚመለስ ብድር አገልግሎት መልኩ ሊሰጥ ይችላል።

ኇ/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ባንክ በብሔራዊ ባንክ ባለ ሂሳብ አነስተኛ መጠባበቂያ እንዲይዝ ሊጠይቅ ይችላል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ የአነስተኛ መጠባበቂያዎች እና የአስተዳደራዊ ቅጣቶችን ስሌት እና አወሳሰን ጨምሮ የብድር፡ የክፍት ገበያ ሥራዎች፣የስታንዲንግ ፋሲሊቲዎች፣ የአጭር ጊዜ ዕዳ ሰነዶች እና የአነስተኛ መጠባበቂያ ገንዘብ መስፈርቶችን የሚመለከቱ ግዴታዎችና ሁኔታዎችን በመመሪያ ይወስናል።

፴. የመጨረሻ አማራጭ አበዳሪ

፩/ብሔራዊ ባንክ ጊዜያዊ የገንዘብ እጥረት የገጠመው ሆኖ ዕዳውን ግን መክፈል ለሚችል ባንክ ጊዜያዊ ብድር ሊሰጥ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ጊዜያዊ ብድር ከገንዘብ ፖሊሲ ተመኖች በላይ የሆነ ወለድ የሚታሰብበት ሆኖ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ የሚጠየቁ የማስተካከያ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ ባንኩ ጊዜያዊ ብድር ስለሚመልስበት የጊዜ ገደብ፣ብብድሩ ዋስትና የሚያቀርበውን የመያዣ አይነት፣ ተጨማሪ ግዴታዎች እና ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

deposit, an overnight lending and intra- day facility.

3/ The National Bank may require a bank to hold minimum reserves on accounts within the National Bank.

4/ The National Bank shall determine by a Directive the terms and conditions for its credit, open market operations, standing facilities, short-term debt instruments, and minimum reserve requirements, including the the calculation and determination of minimum reserves and administrative penalties.

30. Lender of Last Resort

1/ The National Bank may grant temporary advances to a solvent bank that experiences a temporary liquidity problem. Such temporary advance shall bear an interest rate above monetary policy rates and on the condition that a bank implements corrective measures required by the National Bank;

2/ The National Bank shall determine the time limit for temporary advance repayment, the type of collateral provided for the loan by a bank and additional obligations and conditions by a Directive.

ይ/በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ መረጋጋትን ለማስጠበቅ ሲባል በሚኒስቴሩ ይሁንታ ዕዳቸውን መክፈል መቻላቸው አጠራጣሪ ለሆነ ባንኮች ብድር ሊሰጥ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንውስ አንቀፅ ፫ የተመለከተው ቢኖርም የሚሰጠው ብድሩ በብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ አቋም ላይ የሚኖረውን ማንኛውንም አሉታዊ ተፅእኖ ውሰን ለማድረግ መንግሥት ለብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ የሕግ ኣልባሳጅነት ያለው ዋስትና ሲሰዋ ነው።

፭/የተቀባዩ ባንክ ብቁነት፣ የመያዣው በቂነት፣ የሚከፈለው የወለድ መጠን፣ የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲሁም ጊዜያዊ ብድር የሚሰተባቸው ሥነ-ሥርዓቶች ብሔራዊ ባንክ በሚደወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል።

፴፩. ዴሎች ተግባሮችና አገልግሎቶች

፩/ ብሔራዊ ባንክ፡-

ሀ) የፋይናንስ ተቋሙ በተቀበለው ተቀማጭ ገንዘብ ላይ ወይም በሌላ መልኩያ ላይ ተመሥርቶ በማስላት ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በዋሬ ገንዘብ፣ በሌሎች ገንዘብ አከል ንብረቶችና በመንግሥት የዋስትና ሰነድ መልኩ

3/ Notwithstanding sub-article 1 and 2 of this Article, the National Bank for the purpose of maintaining financial stability with the approval of the Ministry, may grant advances to banks whose solvency is in doubt.

4/ The advance provided under sub-article 3 of this Article, shall be granted when the Government provides a prior legally binding guarantee to the National Bank to limit any negative impact of such lending on the National Bank's financial position.

5/ The eligibility of recipient bank, the adequacy of collateral, the amount of interest rates to be charged, corrective measures to be taken, as well as procedures for providing temporary advance shall be determined by a Directive to be issued by the National Bank.

31. Other Functions and Services

1/ The National Bank may:

a) timely determine, on the basis of accessing the received deposit or any other scale, the amount of assets to be held by a financial institution in the form of cash, other liquid assets and government

መያዝ ያለበትን የገብት መጠን ሊወስን እና ይኸው ሀብትም በገንዘቡ እንዲቀመጥ በየጊዜው ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤

ለ) በዚህ ንውስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፋይናንስ ተቋም በአደራ ገንዘብ ተቀብሎ ሊያስቀምጥ እንዲሁም በፋይናንስ ተቋም ስም ወይም ስለእርሱ ሆኖ ገንዘብ ሊቀበል ይችላል፤

ሐ)ለማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የክፍያና የማጣራት አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፤

መ)ለማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ሂሳብ ሊይዝና ወኪል ወይም ተጠሪ ሆኖ ሊሠራ ይችላል።

፪/ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ (፩) ለተጠቀሱት አገልግሎቶች ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል፤ የክፍያውን መጠን ለፋይናንስ ተቋሙ በቅድሚያ ያሳውቃል።

securities; and also timely order the deposit of the same asset with it;

b) without prejudice to sub-article (1 (a)) of this Article, accept money on deposit form, and collect money for and on account of financial institution;

c) provide payments and clearing services to financial institution;

d) keep balances and act as agent or correspondent of a financial institution.

2/The National Bank may charge fees for the services referred to sub-article (1) of this Article. Such fees shall be communicated in advance to the financial institution.

፴፪. የሀገር ውስጥ እና ድንበር ተሻጋሪ ትብብር

32. Domestic and Cross-Border Cooperation

፩/ብሔራዊ ባንክ ተቀናጅቶ እና ተባብሮ በመሥራት እና አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ሥልጣኑን ለመጠቀምና ተግባራቱን ለመወጣት ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ተቆጣጣሪ፣ የሕልባት ወይም የገንዘብ ባለሥልጣን ጋር ስምምነት ማድረግ ይችላል።

1/The National Bank may conclude an agreement with domestic or foreign regulatory, resolution, or monetary authority for the purpose of coordinating, cooperating, and exchanging information relevant for the exercise of its powers and duties.

ሸ/ ብሔራዊ ባንክ ከማንኛውም የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተቀበለው ወይም የተጋራው ማንኛውም መረጃ ለተሰጠበት ዓላማ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

ቀ/ብሔራዊ ባንክ ከውጭ አገር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አካል የተቀበለውን ማንኛውንም ሚስጥራዊ መረጃ በሕግ ካልተፈቀደ ወይም በፍርድ ቤት ካልታዘዘ ወይም የብሔራዊ ባንኩን ጥቅም በፍርድ ሂደት ለማስጠበቅ ካልሆነ በስተቀር ከውጭ አገር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ አስቀድሞ ፈቃድ ሳያገኝ ለሌላ አካል ሊገልጽ አይችልም።

በ/ ማንኛውንም ሚስጥራዊ መረጃ ከብሔራዊ ባንክ በሚቀበል ማንኛውም የሀገር ውስጥ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እና በሥራተኞቹ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል።

፴፫. የክፍያ፣የማጣራት እና የማወራረድ ሥርዓቶች

፩/አግባብነት ያለው ሕግ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ የክፍያ፣ የማጣራት እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማወራረድ ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ በባለቤትነት መያዝ፣ በዚያ መሳተፍ፣ ማንቀሳቀስ፣ መከታተል እና መቆጣጠር ይችላል።

፪/ የክፍያ፣ የማጣራት እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማወራረድ ሥርዓቶችን ደህንነት፣

2/Any information received from or shared with a domestic or foreign authority may only be used for the purpose that such information is provided for.

3/ The National Bank may not disclose any confidential information received from a foreign authority to any other body without the prior consent of the foreign authority, unless such disclosure is required by law or ordered by court or to protect the National Bank's interests in legal proceedings.

4/ Any domestic authority and its officers, receiving any confidential information from the National Bank shall be subject to the provisions of Article 42 of this Proclamation.

33. Payment, Clearing, and Settlement Systems

1/ Subject to pertinent law, the National Bank may establish, own, participate in, operate, supervise, regulate and oversee payment, clearing and security settlement systems.

2/ The National Bank may provide facilities, including intra-day credit to payment, clearing and securities

ጤናማነት እና ቅልጥፍና ለማረጋገጥ ሲባል ብሔራዊ ባንክ ለእነዚህ ሥርዓቶች እና ለተሳታፊዎቻቸው በዕለቱ የሚመለስ ብድርን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን ሊያቀርብ ይችላል።

settlement systems and their participants, to ensure the safety, soundness and efficiency of such systems.

፴፬. የብድር ማመሳከሪያ ሥርዓት እና የፋይናንስ መሰረተ ልማት

34. Credit Reference System and Financial Infrastructure

ብሔራዊ ባንክ፡-

The National Bank may:

፩/ የብድር ማመሳከሪያ ሥርዓትን እና ሌሎች የፋይናንስ መሰረተ ልማቶችን እና የብድር ቢሮዎችን ሊያቋቁም፣ በባለቤትነት ሊይዝ፣ በእነዚህ ስርዓቶች ሊሳተፍ፣ ፈቃድ ሊሰጥ እና ሊቆጣጠር፣ እና

1/ establish, own, participate, license and regulate Credit Reference System, other financial infrastructures and Credit Bureaus; and

፪/ የብድር ማመሳከሪያ ሥርዓት፣ሌሎች የፋይናንስ መሰረተ ልማቶችን እና የብድር ቢሮዎችን አሰራር፣ፍቃድ እና ቁጥጥር የሚያስተዳድር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

2/ issue a Directive to govern the operation, licensing and regulation of Credit Reference System, other financial infrastructures and Credit Bureaus.

ክፍል ሰባት

PART SEVEN

የገንዘብ መደብ ልክና ሕጋዊ ገንዘብ

THE MONETARY UNIT AND LEGAL TENDER

፴፭. የገንዘብ መደብ

35. Monetary Unit

፩/ የኢትዮጵያ የገንዘብ መደብ ብር ሲሆን የሀገሪቱ ሕጋዊ ገንዘብ ይሆናል።የብር አፈሊላዊ አጭር ስያሜ "ብር" የሚል ሆኖ

1/ The monetary unit of Ethiopia shall be Birr and it shall be the legal tender of the country. The official abbreviation of

"ኢትብ" የሚለው የብር ዓለም አቀፋዊ አጭር ስያሜ ይሆናል።

፪/ የገንዘብ መደቡ "ሳንቲሞች" ተብለው በሚጠሩና እኩል በሆኑ አንድ መቶ ክፍልፋዮች ይከፈላል። የሳንቲም አጭር ስያሜ "ሳ" ይሆናል።

፫/ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተደረገ ስምምነት እስካልሆነ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉ ማናቸውም የገንዘብ ስምምነቶችና ውሎች በብር እንደተፈጸሙ ይቆጠራል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ በሌላ አኳኋን ካልፈቀደ ወይም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም የገንዘብ ግንኙነቶች ሁሉ የሚመዘገቡትና የሚከፈሉት በብር ይሆናል።

፴፮. ሕጋዊ ገንዘብ

፩/ብሔራዊ ባንክ በኢትዮጵያ ሕጋዊ ገንዘብ የማውጣት ብቸኛ ሥልጣን አለው።

፪/በኢትዮጵያ ውስጥ በገዘውር ላይ ያሉ ሕጋዊ የብር ኖቶች ሁሉ ማንኛውንም የመንግሥትም ሆኑ የግል ዕዳ ያለባደብ ለመክፈል ሕጋዊ ገንዘብ ናቸው።

፫/በገንዘብ ኖቶች ላይ የሚጻፈው ጽሁፍ፣ የኖቶቹ ስፋት፣ ቅርጽና መደባቸው እንዲሁም ሌሎች ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናሉ።

the Birr shall be "Br", and "ETB" shall be the international currency code.

2/ The Monetary unit shall be divided into one hundred equal parts, named "cents", the official abbreviation of which shall be "Ct".

3/ All monetary transactions taking place in Ethiopia shall be presumed to be expressed in Birr unless validly agreed upon otherwise by the permission of the National Bank.

4/All monetary transactions shall be recorded and settled in Birr unless otherwise authorized by the National Bank or provided for in any international agreement to which Ethiopia is a party.

36. Legal Tender

1/The National Bank shall have the sole authority to issue legal tender.

2/ Birr notes lawfully in circulation within Ethiopia shall be unlimited legal tender in the settlement of all public or private debts.

3/The inscription, dimension, design, denomination and other characteristics of legal tender notes shall be determined by the National Bank.

6/ የቅንስናሽ ገንዘቦች ክብደት፣ ጥራት፣ ጽሁፍ፣ ስፋት፣ ቅርጽና መደብና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናሉ። በተመሳሳይ የመታሰቢያ ሳንቲሞች ሕጋዊ ተቀባይነት፣ ብዛት፣ ክብደት፣ ጥራት፣ ጽሁፍ፣ ስፋት፣ ቅርጽና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናሉ።

6/ The weight, fineness, inscription, dimension, design, denomination and other characteristics of coins shall be determined by the National Bank. Similarly, values of commemorative coins at which they shall be accepted as legal tender, their numbers to be minted, weight, fineness, inscription, dimension, design and other characteristics thereof shall be determined by the National Bank.

7/ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ሆነው በዝውውር ላይ ያሉ ቅንስናሽ ገንዘቦች ማናቸውንም የመንግሥትም ሆነ የግል ዕዳ ለመክፈል ሕጋዊ ገንዘብ ናቸው። ተዋዋይ ወገኖቹ በሌላ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር ዕዳ ለመክፈል የሚውለው ቅንስናሽ ገንዘብ መጠን ከአስር ብር መብለጥ የለበትም። ሆኖም ብሔራዊ ባንክም ሆነ ባንኮች በማንኛውም አምጪ ጥያቄ ቅንስናሽ ገንዘቦቹን ወደ ኖቶች መቀየር አለባቸው።

7/ Coins lawfully in circulation within Ethiopia shall be legal tender in the settlement of all public and private debts. Unless the parties agree otherwise, the amount of coins used for settlement of such debts shall not exceed ten Birr; provided, however, that the National Bank and banks shall, at the request of any holder, change into notes the holder's coins.

8/ በማንኛውም ጊዜ የብር ኖቶችን ወይም ሳንቲሞችን የአስመሳሉ ስራት መከላከያ ግልጽና ስውር ምልክቶች የቀየረ እንደሆነ፣ ወይም በሥራ ላይ የነበረ ኖት ወይም የተለየ መጽሐ ያለው ኖት ወይም ሳንቲም ከተወሰነ ቀን በኋላ ሕጋዊ የመገበያያ ገንዘብነቱ ከቀረ ብሔራዊ ባንክ፡

8/ Whenever the security and features of a particular issue or denomination of notes or coins are changed or a particular issue or denomination of notes or coins cease to be legal tender as of a certain date, the National Bank shall:

ሀ) ቅያሪውን ወይም ሕጋዊ መገበያያ ገንዘብ መሆኑ የቀረውን ኖት ወይም ሳንቲም መመሪያ በማውጣት ያሳውቃል፤

ለ) የተደረገውን ለውጥ በሰፊው በሚሰራጩ ጋዜጦችና በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች ይገልጻል፤

ሐ) የሚለውጡትን ኖቶችና ሳንቲሞች የያዙ ሁሉ በአዲሶቹ ኖቶችና ሳንቲሞች የሚለውጡበት በቂ ጊዜ ይሰጣል።

፯/ ብሔራዊ ባንክ የሕጋዊ ገንዘብ ምስሎችን ለማባዛት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በተመለከተ የመፍቀድ ወይም የመከልከል ብቸኛ ሥልጣን አለው።

፴፯. ከሕጋዊ ገንዘብ ጋር የተያያዙ ክልከላዎች

፩/ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው በላይ የኢትዮጵያን ገንዘብ ይዞ ሀገር ውስጥ ለመግባት ወይም ለመውጣት አይችልም።

ለ) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ብሔራዊ ባንክ ካልፈቀደ በስተቀር ክሪፕቶ-ከረንሲ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዲጂታል ወይም የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ በመጠቀም ክፍያ መፈፀም አይችልም።

a) declare such change or withdrawal by Directive;

b) announce such declaration through newspapers of wider circulation and other communication media; and

c) give to holders of such notes and coins reasonable time to exchange such notes and coins for new ones.

7/ The National Bank has the sole discretion to authorize or refuse the request for the reproduction of images of a legal tender.

37. Prohibitions related to Legal Tender

1/ No person:

a) entering into, or departing from, Ethiopia shall carry with him an amount of legal tender in excess of an amount fixed or permitted by a Directive to be issued by the National Bank.

b) shall make any payments using crypto-currency or any other digital or electronic currency unless permitted by the National Bank when it deems necessary.

ሐ) ከብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ይሁንታ ሳያገኝ እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በብሔራዊ ባንክ የታተመ ሕጋዊ የገንዘብ አካልን ማጥፋት፣ ማጉደል፣ ማቅለጥ፣ በማንኛውም ውህድ ውስጥ ማሟሟት፣ መሰባበር ወይም በማናቸውም መንገድ ማበላሸት የለበትም፣ እንዲሁም ካበላሸ ወይም ካጎደለ በኋላ ማሰራጨት የለበትም።

c) may without the prior written approval of the National Bank, intentionally or negligently destroy, deface, disfigure, mutilate, melt down, dissolves in any dissolvent, breaks up or damages in any way legal tender that has been minted or issued by the National Bank and put in circulation such a legal tender.

መ) ከብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፍቃድ ውጪ የሕጋዊ ገንዘብ ምስልን ማባዛት የለበትም።

d) shall engage in the reproduction of the image of a legal tender without the written authorization of the National Bank.

ሠ) ያለ ሕጋዊ ሥልጣን እያወቀ የሕጋዊ ገንዘብ ወይም የሕጋዊ ገንዘቡን የተወሰነ ክፍል ለማስመሰል ወይም ለማምታታት የሚያስችሉ ሰነዶችን ለማተም ወይም ለማባዛት የሚጠቅም ወይም ሊጠቅም የሚችል ማንኛውንም ዓይነት መሣሪያ በእጁ መያዝ የለበትም።

e) shall without lawful authority, knowingly keeps in his possession any instrument used for or capable of being used for printing or reproducing any document purporting to be or in any way resembling or as to be calculated to deceive, a legal tender or a part of it.

ረ) ያለ ሕጋዊ ሥልጣን እያወቀ ሕጋዊ ገንዘቦች በሚገለጹበት ወረቀት ላይ የሚታዩ እንደ ቃላት፣ ምስል፣ መሣሪያ ያሉ መለያዎች የያዘ ወረቀት ወይም የሕጋዊ ገንዘቡን ሙሉ ወይም የተወሰነ ክፍል ለማስመሰል የተቀረጸ ወይም የተሠራ ቁስ ወይም በሕጋዊ ገንዘቦች

f) shall without lawful authority, make use of or knowingly possess a paper with a word, figure, device or distinction peculiar to and appearing in the substance of the paper used for legal tender or material upon which the whole or part of a legal tender purporting to resemble the legal tender

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

ላይ የሚታይ ፊርማን ቅጂ መጠቀም ወይም እያወቀ መያዝ አይችልም።

has been engraved or made or any facsimile of the signature of any signatory whose signature has appeared on legal tender.

፪/ብሔራዊ ባንክ የሕገ-ወጥን ሕጋዊ ገንዘብ የአካል ጥበቃ ሁኔታ በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

2/ The National Bank may issue Directive to provide the details for the physical protection of the legal tender of the country.

ክፍል ስምንት
ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብና የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር

PART EIGHT
INTERNATIONAL RESERVE FUND AND FOREIGN EXCHANGE ADMINSTRATION

ፀ፰. ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ ስለመያዝ

38.Maintaining International Reserve Fund

፩/ ብሔራዊ ባንክ የውጭ አገር ገንዘብ፣ የግዴታ ሰነዶች፣ ወርቅ ወይም ሌሎች ዓለምአቀፍ መጠባበቂያ ንብረቶችን ያካተተ ሂሳብ ይኖረዋል።

1/ The National Bank shall maintain among its assets an international reserve fund consisting of foreign currencies, foreign securities, gold or other international reserve assets.

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚይዘው ዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሳብ በማናቸውም ጊዜ፦

2/The National Bank shall endeavor to maintain, at all times, sufficient international reserve fund as provided for in sub-article (1) of this Article, to cover:

ሀ) አስቸኳይና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ክፍያን፤

a) payments for immediate and short term imports of commodities and services into the country;

ለ) የውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያ ግዴታዎችን፣ እና

b) foreign debt payment commitments; and

ሐ)የመሠረታዊ አገልግሎቶች ክፍያን፣
በበቂ ሁኔታ ለመሸፈን የሚያስችል እንዲሆን
ጥረት ያደርጋል።

c) payments for basic services.

፫/ የዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ገንዘብ ከሚያስፈልገው መጠን ያነሰ እንደሆነ ወይም ሊያንስ እንደሚችል ገዥው ካመነበት ወይም የመጠባበቂያ ገንዘቡ በቂነት የመሟያስ አዝማሚያ እያሳየ መሆኑን ሲገነዘብ የመጠባበቂያ ገንዘቡን ይዞታ፣ ለውጌታው መንሥኤ የሆኑትን ወይም ሊሆኑ የሚችሉትን ምክንያቶች እና ሁኔታውን ለማሻሻል አስፈላጊ የመሰለውን የመፍትሔ እርምጃ ያካተተ የውሳኔ ሃሳብ የያዘ ሪፖርት ለቦርድ ያቀርባል። ችግሩ እየተባባሰ መሔዱን ከተገነዘበ ገዥው የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዳይሰጥ ሊያግድ ይችላል።

3/ If the international reserve has declined or, in the opinion of the Governor, appears to be in danger of declining or is at such a level that the Governor considers its adequacy in jeopardy, the Governor shall submit a report to the Board on the international reserve fund position and the causes that have led to, or may lead to, such a decline, together with recommendations concerning the measures the Governor considers necessary to forestall or otherwise remedy the situation. When the situation persists, the Governor may decline issuance of further foreign exchange permit.

፬/ ብሔራዊ ባንክ ሰባንኩና ሰሀገሪቱ ጠቃሚ ሆነው የሚታዩትን የኮስትዮሽና ሌሎች ዓለም አቀፍ የገንዘብና የክፍያ እንዲሁም ተዛማጅ ስምምነቶች ሊዋዋል ይችላል።

4/The National Bank may enter into bilateral or other international monetary, payment and related agreements which it deems are in the interest of the Bank and the country.

፴፱. የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር

39. Regulation of Foreign Exchange

፩/ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲውን ከውጭ ምንዛሪ ሥርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ እና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ስምምነቶች ላይ

1/ The National Bank shall implement its foreign exchange policy in line with the foreign exchange regime, while having due regard to the obligations which

የገባችውን ግዴታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ ያደርጋል።

፪/ ማንኛውም ሰው ከባንኮች ወይም ሥልጣን ከተሰጣቸው መንዛሪዎች ጋር ካልሆነ ወይም ከብሔራዊ ባንክ የተለየ ፈቃድ ካላገኘ በቀር በውጭ ምንዛሪ ግብይት ለመሰማራት አይፈቀድለትም።

፫/ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ፣ ነዋሪ ያልሆኑና ለጉብኝት የመጡ ሰዎች ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው የውጭ ምንዛሪ የሚይዝበት ወይም በውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚፈጽምበትን ወይም የክፍያ ማዘዣዎችን የሚይዝበትንና የሚጠቀምበትን ሁኔታዎችና ገደቦች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፬/የውጭ ምንዛሪ ወደ ኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ውጪ የሚተላለፍባቸው፣ በወጪ ወይም በገቢ ንግድ አማካኝነት ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ወደ ውጭ የሚላኩባቸው ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡባቸው ወይም ሌሎች ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች በማናቸውም አኳኋን የኢትዮጵያን የጉምሩክ ድንበር አቋርጠው የሚተላለፉባቸው፣ እንዲህ ያሉት ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚመለሱባቸው እና ከላይ ለተመለከቱት ወደ ውጭ የተላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ወይም ከውጭ

Ethiopia has assumed in accordance with the provisions of international monetary agreements to which it is a party.

2/ No person shall engage in any transaction of foreign exchange except with banks or authorized dealers or with the special permission of the National Bank.

3/ The conditions, limitations and circumstances under which residents of Ethiopia, and non- residents visiting Ethiopia, or any other person may possess and utilize foreign currency or instruments of payments in foreign exchange shall be determined by Directive to be issued by the National Bank.

4/ The terms and conditions for transfer of foreign exchange to and from Ethiopia, and the export or import of valuable goods or the transfer of other valuable goods across the customs boundaries or frontiers of Ethiopia in any manner, the return of such goods and the settlement of any foreign exchange that results, or that will result, from such export or import or transfer shall be determined by Directive to be issued by of the National Bank.

የተመለሱ ዕቃዎች በሙሉ ምንዛሪ ክፍያ የማፈጸምባቸው ግዴታዎችና ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

5/ Goods shall be imported on franco-valuta basis in accordance with the terms, circumstances and conditions to be determined by National Bank's Directive

፮/ዕቃዎች ያለሙሉ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት የሚችሉት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚወሰኑ ግዴታዎች እና ሁኔታዎች መሠረት ነው።

6/ The Ethiopian Customs Commission or a government body for the time being responsible for matters relating to customs, shall not allow import or export of valuable goods or foreign exchange unless conditions, circumstances and terms determined by the National Bank are fulfilled.

፯/ብሔራዊ ባንክ የደንጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን ክላሪ ጋነጠ በስተቀር የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ወይም በጊዜው ከጉምሩክ ጋር በተያያዘ ሥልጣን ያለው የመንግሥት አካል፣ ማንኛውም ዋጋ ያለው ዕቃ ወይም የውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ወይም እንዲገባ አይፈቅድም።

7/ The National Bank shall monitor foreign exchange transactions of financial institution through on-site inspection or off-site surveillance.

፰/የፋይናንስ ተቋማት በሙሉ ምንዛሪ የሚያደርጉትን ልውውጥ ወይም ግብይት ብሔራዊ ባንክ በዐይታው ተገኝቶ በመመርመር ወይም በሚቀርቡለት መረጃዎች መሠረት በመከታተል መቆጣጠር አለበት።

8/ Any bank, insurance company, authorized dealer or any other person shall, when directed by the National Bank, produce to it or its designated representative all information, books, records, accounts and other documents in its possession or control which may

፰/ማንኛውም ባንክ፣ የመድን ሰጪ ኩባንያ፣ ሥልጣን የተሰጠው መንዛሪ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅና የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ድንጋጌዎችን መፈጸም ወይም አለመፈጸማቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል በእጁ የሚገኙትን ወይም የሚያዘባቸውን ማናቸውንም መረጃዎች፣

የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ሰነዶች በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ለባንኩ ወይም ባንኩ ለመደበው ወኪል ማቅረብ አለበት።

be required for the purpose of ascertaining whether or not the provisions of this Proclamation and Directives issued by the National Bank are complied with.

፵.በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ንብረቶች ስለሚደረግ ግብይት

40 Transactions in International Reserve Assets

፩/ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ሀገር የገንዘብ ኖቶች እና ቅንስናሽ ገንዘቦች እንዲሁም በዓለም አቀፍ ክፍያ ወይም ለገንዘብ ማስተላለፊያነት በተለምዶ የሚሠራባቸውን የገንዘብ ማዘዋወሪያና ሌሎች ሰነዶች፣ ሐዋላዎች የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለመግዛት፣ ለመሸጥና ለመያዝ ይችላል

1/ The National Bank may buy, sell and hold foreign currency notes and coins and such other documents and instruments using various media as are customarily employed in international payments or transfers of funds.

፪/ ብሔራዊ ባንክ በውጭ ሀገር ማዕከላዊ ባንኮች፣ በራሱ ወኪሎች ወይም የውጭ ተጠሪ ባንኮች ዘንድ በውጭ ሀገር ገንዘብ ሂሳብ ሊኖረውና ይህንንም ገንዘብ እንደአስፈላጊነቱ በጊዜ ገደብ ተቀማጭ፣ በወርቅ፣ በቀላሉ ሊተላለፉ በሚችሉ የውጭ ሀገር የዋስትና ሰነዶችና በሌሎች ኢንቨስትመንቶች ሊያውል ይችላል።

2/ The National Bank may keep balances, denominated in foreign currencies, with foreign central banks, its agents or correspondents abroad, and may invest, at its discretion, such balances in time deposits, gold, readily negotiable foreign securities and other investment instruments.

፫/ ብሔራዊ ባንክ፦

3/ The National Bank may engage in foreign exchange transactions with the following:

ሀ)ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የፋይናንስ ተቋማት፣

a) financial institution in Ethiopia;

ለ)ከመንግሥት፣ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ተቋሞች፣

b) the Government, its agency, and institution;

ሐ)ከውጭ ሀገር ማዕከላዊ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋሞች፣

መ) ከውጭ መንግሥታትና መሥሪያ ቤቶቻቸው፣ እና

ሠ) ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት፣ ጋር የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ሥራ ሊሠራ ይችላል።

፬/ሌላ ተቃራኒ የሕግ ድንጋጌ ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ በራሱ ውሳኔ ብቻ ወርቅና ብር የመሳሰሉ የከበሩ ማዕድናት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለመግዛት፣ ለመሸጥ፣ ለማስቀመጥ ወይም በሌላ ሁኔታ ለመገበያየት ይችላል።

፭/ ብሔራዊ ባንክ፡-

ሀ) የፋይናንስ ተቋምና ሥልጣን የተሰጣቸው መንዛሪዎች በውጭ ምንዛሪ፣ በወርቅ ወይም በብር ግብይት እንዲሳተፉ ሥልጣን ሊሰጣቸው ይችላል፤

ለ) የውጭ ምንዛሪ፣ የወርቅና የብር ግብይትን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

ሐ) የፋይናንስ ተቋማት የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዲሰጡ ሊወክላቸው ይችላል።

c) foreign central banks and financial institution;

d) d)foreign government and agency; and

e) international financial institution.

4/ Notwithstanding any other contrary provisions of law, the National Bank may at its sole discretion, import, export, buy, sell, hold or otherwise deal in precious metals such as gold and silver.

5/ The National Bank may:

a) appoint financial institutions and authorized dealers to engage in transactions involving foreign exchange, gold or silver;

b) issue Directive relating to transactions in foreign exchange, gold or silver;

c) delegate financial institution to issue foreign exchange permits.

ክፍል ዘጠኝ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፵፩. የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ጥበቃ

፩/ የፋይናንስ ተቋማት ከፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ሁሉ ፍትሀዊ እና ምክንያታዊ መሆን አለባቸው።

፪/ የፋይናንስ ተቋማት፦

ሀ) የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ማስፈራራትን፣ ማሸማቀቅን፣ ኃይል መጠቀምን፣ ማንገላታትን፣ ማዋረድን የመሳሰሉ ፍትሃዊነት የጎደላቸው፣ አሳሳች ወይም ነውጠኛ ድርጊቶችን መፈጸም አይችሉም፣ እና

ለ) በማንኛውም የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ላይ ፆታን፣ ዘርን፣ ብሔርን፣ ሀይማኖትን፣ የፖለቲካ አመለካከትን ወይም የአካል ጉዳትን መሠረት ያደረገ መድሎ መፈጸም አይችሉም።

፫/ የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከፋይናንስ ተቋማት ጋር አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ የመደመጥ መብት አላቸው።

፬/የፋይናንስ ተቋማት የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቅሬታዎች ለመቀበል፣ለመመር መር እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ አሠራሮችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ማዋል አለባቸው።

PART NINE

MISCELLANEOUS PROVISIONS

41. Financial Service Consumer Protection

1/ Financial institutions shall act fairly and reasonably in all their dealings with financial service consumers.

2/ Financial institutions shall not:

a) engage in unfair, deceptive or aggressive practices such as threatening, intimidating, violent, abusing or humiliating financial service consumers; and

b) discriminate against any financial service consumer on the grounds of sex, race, ethnic origin, religion, political outlook or disability.

3/ Financial service consumers have the right to be heard in case of disagreement with financial institutions.

4/Financial institutions shall have in place and operate appropriate and effective procedures, for receiving, considering and responding to complaints of their financial service consumers.

ሯ/ የሚኒስትሮች ምክር በት የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ጥበቃ እና የፋይናንስ ቅሬታ አያያዝ ወሰን እና አሰተዳደርን የሚመለከት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፵፪. መረጃን ስለመሰብሰብ እና ስለመስጠት

፩/ ብሔራዊ ባንክ ሥልጣኑንና ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስፈልገውን ማንኛውንም መረጃ ከፋይናንስ ተቋማትም ሆነ ከሌሎች ማናቸውም ሰዎች የመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቶታል።በብሔራዊ ባንክ መረጃ አንዲሰጥ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ተገቢውን መረጃ ብሔራዊ ባንክ በጠየቀበት አግባብና ጊዜ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፪/ መረጃው የሚሰጠው፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ለማስፈጸም፣

ለ) የፋይናንስ ሥርዓቱን ጤናማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ) መረጃውን ለመቀበል ሕጋዊ ሥልጣን ላላቸው ሰዎች፣

5/The Council of Ministers may issue a Regulation pertaining to scope and governance of financial service consumer protection and financial complaint handling.

42 Collecting and Disclosure of Information

1/ The National Bank is empowered to collect any information from financial institutions and any other persons, as it may deem necessary to implement its powers and duties. Any person receiving any such request from the National Bank is under an obligation to furnish the relevant information within the time and in the manner prescribed by the National Bank.

2/ The National Bank shall not disclose the information it collected using its authority under sub-article 1 of this Article to any person, whether within or outside Ethiopia unless the disclosure is:

a) for the purpose of fulfilling the requirements of this Proclamation;

b) required to ensure soundness of the financial system;

c) made to recipients who are legally authorized to obtain such information;

መ) ብሔራዊ ባንክ ተጠሪ ለሆኑለት አካል፣

d) made to the body to which the National Bank is accountable;

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ መሠረት ለሀገር ውስጥ ወይም ለውጭ ሀገር ተቆጣጣሪ፣ የክትትል፣ የእልባት ወይም የገንዘብ ባለሥልጣናት፣

e) provided to domestic or foreign regulatory, supervisory, resolution or monetary authorities, subject to Article 32 of this Proclamation;

ረ)በፍርድ ሂደት የብሔራዊ ባንክን ጥቅም ለማስከበር፣

f) required by the interests of the National Bank in legal proceedings;

ሰ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ ወይም

g) ordered by a court; or

ሸ)ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች የገባችባቸውን ግዴታዎች ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣

h) required for the purpose of meeting obligations which Ethiopia entered into under international agreements.

ካልሆነ በስተቀር ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሰበሰባቸውን መረጃዎች በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚገኝ ለማንም ሰው አሳልፎ አይሰጥም።

፫/በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ የተጣለን ግዴታ ለመፈፀም ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የቦርድ አባል፣ ገዥ፣ ምክትል ገዥ ወይም ሠራተኛ ሆኖ እያገለገለ ያለ ወይም ያገለገለ ሰው፡-

3/ Except when necessary to fulfill any duty imposed by this Proclamation or any other law, no person who serves or has served as a member of the Board, Governor, Vice Governor, or employee shall:

ሀ) ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ ያገኘውን ሚስጥራዊ መረጃ ሌላ ሰው እንዲጠቀም መፍቀድ፣ማውጣት ወይም ማተም፤ ወይም

a) permit access to, disclose or publicize confidential information which he has obtained in the exercise of his duties; or

ለ) እነዚህን መረጃዎች ለግል ጥቅም ማዋል ወይም እንዲውሉ መፍቀድ፣ አይችልም።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ የተመለከተው ክልከላ ብሔራዊ ባንክ ላይ የተጣለበትን ማንኛውም ኃላፊነት ለመወጣት ሲባል የብሔራዊ ባንክ እንደራሴ፣ ባለሙያ፣ አቅራቢ ወይም አገልግሎት ሰጪ ሆኖ በሚሠራ ማንኛውም ሶስተኛ ወገን ላይም ተፈፃሚ ይሆናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ የተደነገገው ቢኖርም ሚስጥራዊ መረጃዎች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሚከተሉት ሁኔታዎች ከብሔራዊ ባንክ ውጭ ለሶስተኛ ወገን ሊገለጹ ይችላሉ፣

ሀ) መረጃው የሚመለከተዉ ሰው መረጃው ለሶስተኛ ወገን እንዲሰጥ በጽሑፍ ግልጽ ፈቃድ የሠጠ እንደሆነ፣

ለ) ሕግ አስከባሪ አካላትን ለመርዳት ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የሚሰጥ መረጃን ጨምሮ መረጃ የመስጠት የሕግ ግዴታን ለመወጣት፣

ሐ) ለብሔራዊ ባንክ የውጭ ኦዲተሮች።

፮/ በብሔራዊ ባንክ ይዞታ ሥር ያሉ ወይም የተዘጋጁ ሰነዶች ሚስጥራዊ ተደርገው የሚመደቡበትን ሁኔታ እና ተደራሽነታቸውን በተመለከተ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

b) use such information, or allow such information to be used, for personal gain.

4/ The prohibition stated under sub- article 3 of this Article, shall also apply to any third person with whom the National Bank engages as an agent, expert, supplier or service provider, for the fulfillment of any responsibility imposed on the National Bank.

5/ Notwithstanding sub- article 3 and 4 of this Article, such persons may disclose confidential information outside the National Bank, in accordance with a Directive to be issued by the National Bank, if such disclosure:

a) is made in accordance with the express consent of the person about whom the information relates;

b) fulfills a duty to disclose as imposed by law, including to assist law enforcement or on the order of a court;

c) is made to the External Auditors of the National Bank.

6/ The National Bank shall determine by a Directive the classification and accessibility of documents held by or drawn up by the National Bank.

፴፫. መረጃ የመስጠት ግዴታ

፩/ ይህን አዋጅ ወይም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ማናቸውንም የብሔራዊ ባንክ ሕጎች በመተላለፍ ሕገወጥ የገንዘብ ሕትመት፣ ሕገወጥ የውጭ ምንዛሪ እና የወርቅ ግብይት ወይም ሌሎች ሕገወጥ ተግባራት ስለመፈጸማቸው መረጃ ያለው ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ ወይም ለሌሎች ሕግ አስከባሪ አካላት ማሳወቅ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለብሔራዊ ባንክ ወይም ለሌሎች ሕግ አስከባሪ አካላት የተሰጠ መረጃ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ንብረት ለመውረስ የሚያደርስ ከሆነ መረጃ እና ድጋፍ የሰጠው ሰው ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሸለማል።

፴፬. የጥቅም ግጭት

፩/ማንኛውም የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ በማንኛውም ጊዜ ከሙያዊ ግዴታው ጋር የጥቅም ግጭት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ሁኔታዎች መራቅ እና በሥራው ሂደት የሚያጋጥመውን የጥቅም ግጭት ለባንኩ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ

43.Obligation to Provide Information

1/ Any person who has information about counterfeiting of legal tender, black market operations related to foreign currency and gold or other illegal activities committed in contravention of this Proclamation and any other relevant laws of the National Bank shall immediately inform the National Bank or other law enforcement bodies.

2/ Where the information provided to the National Bank or other law enforcement bodies pursuant to sub-article (1) of this Article leads to confiscation of the property with which the crime is committed, a person that has provided information and support shall be rewarded in accordance with a Directive to be issued by the National Bank.

44.Conflict of Interest

1/An employee of the National Bank should always avoid situations which may give rise to conflict of interests with his professional duty; and shall promptly disclose to the Bank any conflict of interest that may arise in the course of his duty.

2/ Without prejudice to the generality of sub- article 1 of this Article,the National Bank may issue Directive to govern the

ከዋቅም ግጭት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች የሠራተኞቹን አሠራር የሚቆጣጠር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

conduct of its employees in matters related to conflict of interests.

፵፭. ከግል ተጠያቂነት ስለመጠበቅ

፩/ይህንን አዋጅ እና ከብሔራዊ ባንክ ሥልጣንና ተግባር ጋር የሚገናኙ ሌሎች ሕጎችን ለማስፈፀም ሲባል የብሔራዊ ባንክ ቦርድ አባል ወይም ሠራተኛ ወይም እንደራሴ በቅን ልቦና ለሚፈጽሙው ማናቸውም ድርጊት በገፌ በዕዳ ሊጠየቅ፣ ወይም ማናቸውም ሌላ ዋያቄ ሊቀርብበት አይችልም። ይህ ድንጋጌ በማንኛውም የብሔራዊ ባንክ የቀድሞ ገዥ፣ ምክትል ገዥ፣ የቦርድ አባል፣ ሠራተኛ ወይም ተወካይ ላይ እኩል ተፌፃሚ ይሆናል።

45.Protection from Personal Liability

1/ Any Board member, employee or agent of the National Bank may not be subject to any personal liability or any other claim for their bona fide acts done for the purpose of carrying out this Proclamation and other laws related to the authority and functions of the National Bank. This provision equally applies to any former Governor, Vice Governor, Board member, employee or agent of the National Bank.

፪/ በዚህ አንቀፅ ስፌጸጸም ሲባል ከዚህ በላይ የተገለጹት ሰዎች ሥራቸውን በቅን ልቦና ያለመሥራታቸው በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ካልተረጋገጠ በቀር፣ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ስፌጸሙት ወይም ላልፌጸሙት ተግባር ተከሰው ክሱን ሲከላከሉ ለሚያወጡት ሕጋዊ ወጪ ካሳ ይከፌላቸዋል። ቦርዱ የወጪ ዓይነቶችን እና የአከፋፈል ሥርዓታቸውን ስመወሰን መመሪያ ያወጣል።

2/ For the purposes of this Article, the above mentioned persons will be entitled to be indemnified for legal expenses incurred by them while defending against a lawsuit or claim for their actions or inactions in the discharge of their duties, provided that no final court ruling has ascertained they did not act in a bona fide manner. The Board shall issue Directive in order to define the types of expenditure incurred and the defrayal procedures.

፵፮. ከግብር እና ከጻኝነት ክፍያዎች ነፃ ስለመሆን

በሌሎች ሕጎች ከነፃ ነፃ ስለመሆን የተደነገገው

46.Exemption from Tax and Court Fees

Without prejudice to any exemptions from payment provided under other laws, the

እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ፡-

፩/ ከውጭ ሀገር በሚያስገባቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ገንዘብ ኖቶች፣ ሳንቲሞች እንዲሁም የመንገደኞች ቼኮች ላይ ሊጣል ከሚችለው የገቢ ግብር፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ እንዲሁም ከማናቸውም ቴምብር ቀረጥ፣ የከተማ መሬት ኪራይና የከተማ ቤት ግብር ወይም ከንብረት ግብር ወይም ከጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ ነፃ ነው፤

፪/ ወርቅና ብር፣ የአገር ውስጥና የውጭ ምንዛሪ ኖቶችና ሳንቲሞች ወደ አገር ውስጥ ሲያስገባ ወይም ወደ ውጭ ሲልክ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ለመሙላት አይገደድም፤

፫/አግባብነት ባለው ሕግ ከሚጠየቀው የዳኝነት ክፍያ ነፃ ነው።

፵፯. <u>የንብረት ግዥ እና አወጋገድ</u>

ብሔራዊ ባንክ የራሱን የግዥ፣ የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ ዘዴ በመመሪያ የመወሰን ሥልጣን አለው።

፵፰. <u>የማዕከላዊ ባንክ ዲጂታል ገንዘብ</u>

፩/ ብሔራዊ ባንክ እንደ ሕጋዊ የሀገሪቷ መገበያያ ገንዘብ የሚቆጠር የማዕከላዊ ባንክ ዲጂታል ገንዘብ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ቦርዱ የማዕከላዊ ባንክ ዲጂታል ገንዘብ አሠራርን የተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

National Bank shall be exempted from:

1/ the payment of income tax, value added tax, turnover tax, stamp duty, urban land rent and urban house tax or any other property tax, customs duty and tax in respect of local and foreign currency notes and coins it imports and traveller's checks;

2/ making customs declaration when importing or exporting gold and silver, and local and foreign currency notes and coins;

3/ the payment of court fee required by relevant law.

47. <u>**Procurement and Disposal of Property**</u>

The National Bank shall have the authority to determine by a Directive its own procurement, property management and disposal system.

48. <u>**Central Bank Digital Currency**</u>

1/ The National Bank may issue Central Bank Digital Currency as a legal tender of the country.

2/ The Board may issue a Directive for the operation of Central Bank Digital Currency.

፵፱. ስለመራተኞች አስተዳደር

የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞችና የሥራ አመራር አባላት አስተዳደር በቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይዘየርዳል።

፶. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

፩/ከዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ መሠረት አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ቢባልም እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገው የብሔራዊ ባንክ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አግባብነት ያላቸው የፋይናንስ ተቋማት ሕጎችን በማሰ የፋይናንስ ተቋም እና/ወይም በተቋሙ ዳይሬክተሮች፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች ወይም ከፍተኛ የሥራ አስፈፃሚ ኃላፊዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚይስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም በጊዜአዊነት የፋይናንስ አመራር ሥርዓት ችግር ካጋጠመው እና ይህም በአገራቱ ደህንነት እና የፋይናንስ መረጋጋት ላይ ወዲያውኑ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ከሆነ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ ተቋሙ ሥርዓት ቢበዛ ለ፭ ቀናት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ እንዲታገድ ሊያዝ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ፈንድ፣ ሂሳብ ወይም ማንኛውም የፋይናንስ ግብይት

49. Staff Regulations

The employees and management staff of the National Bank shall be administered by a Directive to be issued by the Board.

50. Administrative Sanctions

1/ Notwithstanding criminal conviction of a person under Article 51 of this Proclamation, and without prejudice to the exercise of the National Bank's powers as provided under the relevant laws, the National Bank may issue Directive to impose administrative sanctions on a financial institution and/or its directors, chief executive officers or senior executive officers for breach of respective laws of financial institutions when it deems necessary.

2/ When a financial institution temporarily encounters an operational failure of system which may result into immediate threat to the safety, security and financial stability of the country, the National Bank may partially or totally order for suspension of that system of a financial institution for a maximum of 5 days.

3/ Notwithstanding to sub-article (2) of this Article, National Bank may order the freezing of any fund, account or any

ብሔራዊ ባንክ ኢትዮጵያ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

ከወንጀል ድርጊት ጋር ግንኙነት አለው ብሎ በጠረጠረ ጊዜ ፌንዱ፣ ሂሳቡ ወይም ማንኛውም የፋይናንስ ግብይት ቢበዛ ለ፮ ቀኖት ታግዶ እንዲቆይ በማዘዝ በዚህ አግባብ የወሰደውን እርምጃ ወዲያውኑ ለፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት እና ለሌሎች የሚመለከታቸው ሕግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት ሊያደርግ ይችላል።

financial transaction when such a fund, account or any financial transaction reasonably suspected to be related to criminal activities for a maximum of 10 days and promptly report such action to the Financial Intelligence Service and other relevant law enforcement organs.

፬/ የሚመለከተው የሕግ አስከባሪ አካል በባንኩ የተሰጠው የፅንድ ትዕዛዝ እንዲጸና እና እንዲራዘም በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

4/ The relevant law enforcement organ may as appropriate institute to a court that has jurisdiction for confirmation and extension of freezing within the period indicated in sub-article (3) of this Article.

፭/ በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ መመሪያዎች ላይ የውጭ ምንዛሪ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አፈፃፀምን ማሰናከል የሚያስከትሉትን አስተዳደራዊ ቅጣት ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

5/ The National Bank may issue a Directive to impose administrative penalties when foreign exchange provisions of this Proclamation and Directives are obstructed.

፶፩. <u>ስለ ቅጣት</u>

51.<u>Penalties</u>

፩/ ማንኛውም ሰው፡-

1/ Whosoever:

ሀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በእዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ፡-

a) in violation of the provisions of this Proclamation or Regulations or Directives issued pursuant to this Proclamation:

(፩)በውጭ ምንዛሪ ግብይት የተሳተፈ ወይም የውጭ ምንዛሪ ሲገኝ ወይም ለማግኘት መብት እንዳለው ሲያውቅ ለባንክ ወይም

i/ engages in transactions of foreign exchange or fails to declare to a bank or authorized dealer when he acquires foreign exchange or

ሥልጣን ለተሰጠው መንግሥ ያላሳወቀ እንደሆነ፤

the right to receive foreign exchange;

(፪)የውጭ ምንዛሪ የተቀበለ ወይም በውጭ ምንዛሪ ክፍያ የፈጸመ እንደሆነ፤

ii/ receives or effects payments in foreign exchange;

(፫)የውጭ ምንዛሪ የሚቀበልበትን ጊዜ ያዘገየ ወይም የመቀበል መብቱን የተወ እንደሆነ፤

iii/delays his receipt or extinguishes his right to receive foreign exchange;

(፬)በብሔራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የኢትዮጵያ ገንዘብ ይዞ ከኢትዮጵያ የወጣ ወይም ለመውጣት የሞከረ ወይም የገባ ወይም ለመግባት የሞከረ እንደሆነ፥ ወይም

Iv/ leaves or attempts to leave or enters or attempts to enter Ethiopian territory carrying Ethiopian currency in excess of the amount fixed or authorized by the National Bank; or

(፭)በብሔራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የውጭ ምንዛሪ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፤

v/ is found carrying foreign exchange in excess of the amount fixed or authorized by the National Bank;

ለ)የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በእዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ወይም አተገባበራቸውን ለማዛባት በማሰብ ማናቸውንም ሰነድ ያጠፋ፥ የቀደደ፥ ይዘቱን የቀየረ፥ የደለዘ ወይም የደበቀ ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ ያቀረበ ወይም ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ እንደሆነ፤

b) with intent to evade the provisions of this Proclamation or Regulations or Directives issued pursuant to this Proclamation or to distort their application destroys, tears apart, alters, deletes or hides a document or produces false evidence or makes false declaration

ሐ)በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵፪ የተደነገገውን በመተላለፍ ማናቸውንም መረጃ ለማይገባቸው ሰዎች የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

c) discloses information in violation of Article 42 of this Proclamation; or

መ) ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በማንኛውም ሌላ መንገድ የተላለፈ ወይም አተገባበራቸውን ያሰናከለ እንደሆነ፣ ወንጀል የሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

d) in any other manner violates or obstructs the implementation of this Proclamation or Regulations or Directives issued pursuant to this Proclamation; shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be punishable in accordance with the provisions of the Criminal Code.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት በወንጀል ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

2/ Unless a higher penalty is applicable under the Criminal Code pursuant to sub- article (1) of this Article:

ሀ) ወንጀሉ የተፈጸመው ሥልጣንን አለአግባብ በመጠቀም ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትን ለማካበት ወይም በተደጋጋሚ ሲሆን ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከ፲፭ ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ፶ ሺ. አስከ ብር ፩ ሺ. የገንዘብ መቀጫ ይሆናል፤

a) thepunishment shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be rigorous imprisonment not exceeding 15 years and fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 100,000 where the accused misused the power of his official position or where he committed the offence with intent to improperly amass wealth or where the offence is committed repeatedly;

ለ) የወንጀል ድርጊቱ ከገንዘብ፣ ከወርቅ፣ ከዋስትና ሰነድ፣ ከዕቃ ወይም ከማናቸውም ሌላ ንብረት ጋር የተያያዘ ሲሆን ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱና የእስራት ቅጣቱ እንደተጠበቀ

b) where the offence is connected with currency, gold, security, goods or any other property, the fine shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is

ሆኖ የገንዘብ ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) መሠረት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር እስከ ንብረቱ ዋጋ ሶስት እጥፍ ድረስ ከፍ ሊደረግ ይችላል፤

ሐ)ወንጀሉ የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት ሲሆን ወንጀሉ የተሠራበት ንብረት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) መሠረት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር ድርጊቱ ከተፈጸመበት ወርቅ፣ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነድ፣ ዕቃ ወይም ሌላ ንብረት ዋጋ እስከ ስድስት እጥፍ ድረስ ከፍ ሊደረግ ይችላል፤

መ)የገቢ ወይም የወጪ ንግድ ዕቃዎችን ዋጋ ከተገለጸው ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ያቀረበ ማንኛውም ሰው፣ ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ፀ) (ሀ) ከተመለከተው የገንዘብ ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር ድርጊቱ ከተፈጸመበት ንብረት ዋጋ እስከ ሶስት እጥፍ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣትና ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

ሠ)ወንጀሉ የተፈጸመበት ንብረት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የተወሰነውን የጥሬ ገንዘብ ማውጣትና የመያዝ ገደቦች የጣሰ እንደሆነ ከሶስት ዓመት

committed and the punishment of imprisonment, not exceed three times the value of the property unless it is lower than that imposed under paragraph (a) of this sub-article.

c) where the offence is committed by a body corporate, the fine may, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be raised to six times the value of gold, currency, security, goods or any other property with which the offence is committed unless it is lower than that imposed under paragraph (a) of this sub-article.

3/Whosoever commits over or under invoicing of imported or exported goods shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be punishable with fine up to three times the value of the property unless it is lower than the fine specified under sub-article (2)(a) of this Article, and with rigorous imprisonment from 15 to 25 years.

4/Whosoever contravenes the cash withdrawal and holding limits determined by the National Bank's Directive, without prejudice to the confiscation of the

በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፭/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴፯ (፩) (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ) እና (ረ)) እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ)ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃድ ካልሰጠ በቀር በክሪፕቶ- ከረንሲ ወይም በሌላ ማንኛውም የዲጂታል ወይም የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ማንኛውንም ክፍያ የፈጸመ፤

ለ) ከብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ይሁንታ ሳያገኝ እያወቀ በብሔራዊ ባንክ የታተሙ ሳንቲሞችን ወይም ሕጋዊ የገንዘብ አካልን ያጠፋ፣ ያጎደለ፣ ያቀለጠ፣ በማንኛውም ውህድ ውስጥ ያሟሟ፣ የሰባበረ ወይም በማናቸውም መንገድ ያበላሸ፣ እንዲሁም ካበላሸ ወይም ካጎደለ በኋላ ያሰራጨ፣

ሐ)ከብሔራዊ ባንክ የጽሁፍ ፍቃድ ሳይሰጠዉ የሕጋዊ መገበያያ ገንዘብ ምስል ያባዛ፣

መ)ያለ ሕጋዊ ሥልጣን እያወቀ የሕጋዊ መገበያያ ገንዘብን የተወሰነ ክፍል

property with which the offence is committed, is punishable with simple imprisonment for a period not exceeding three years or a fine not exceeding ten thousand Birr.

5/Whosoever in violation of Article 37 (1(b), 1(c), 1(d), 1(e), 1(f) of this Proclamation and Regulations or Directives issued pursuant to this Proclamation:

a) makes any payments using crypto-currency or any other digital or electronic currency unless permitted by the National Bank when it deems necessary;

b)without the prior written approval of the National Bank, intentionally destroys, defaces, disfigures, mutilates, melt down, dissolves in any dissolvent, breaks up or damages in any way a legal tender that has been minted or issued by the National Bank and put in circulation such a legal tender;

c) without the written authorization of the National Bank, engage in the reproduction of the image of a legal tender;

d) without lawful authority knowingly keeps in his possession any

ለማስመሰል ወይም ለማምታታት የሚያስችሉ ሰነዶችን ለማተም ወይም ለማባዛት የሚጠቅም ወይም ሊጠቅም የሚችል ማንኛውንም ዓይነት መሣሪያ በእጁ ይዞ የተገኘ፣

ሠ) ያለ ሕጋዊ ሥልጣን እያወቀ ሕጋዊ መገበያያ ገንዘብ በሚገለጽበት ወረቀት ላይ የሚታዩ አንደ ቃላት፣ ምስል፣ መሣሪያ ያሉ መለያዎች የያዘ ወረቀት ወይም የገንዘብ ኖቱን ሙሉ ወይም የተወሰነ ክፍል ለማስመሰል የተቀረጸ ወይም የተሠራ ቁስ ወይም የገንዘብ ኖቶች ላይ የሚታይ ፊርማን ቅጂ የተጠቀመ ወይም እያወቀ የያዘ፣

ወንጀሉ የተፈጸመበት ንብረት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፮/ በዚህ አንቀፅ የተመለከተው ማንኛውም የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት ከሆነ የወንጀል ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ድርጅቱን ይመራ የነበረው ዳይሬክተር ወይም ባለሥልጣን ድርጅቱ ድርጊቱን መፈጸሙን እንደማያውቅና በተገዚው ኖሪተም

instrument used for, or capable of being used for, printing or reproducing any document purporting to be or in any way resembling or as to be calculated to deceive, a legal tender or a part of a legal tender;

e) without lawful authority makes use of or knowingly possess a paper with a word, figure, device or distinction peculiar to and appearing in the substance of the paper used for legal tender or material upon which the whole or part of a legal tender purporting to resemble legal tender has been engraved or made or any facsimile of the signature of any signatory whose signature has appeared on legal tender;

without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, is punishable with simple imprisonment for a period not exceeding three years and a fine not exceeding ten thousand Birr.

6/Where any offence under this Article is committed by a body corporate, the director or any other official who was, at the time of the commission of the offence, responsible for the management of the body corporate shall be jointly liable and

ሲያውቀው ኩነኔያዊ ቸልተኝነት በበደለ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር ከድርጅቱ ጋር ተጠያቂ በመሆን ከሰባት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፶ ሺ እስከ ፪ ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፯/ የወንጀሉ ድርጊት የተፈጸመው የህግ ሰውነት ባለው ድርጅት ሠራተኛ ወይም ወኪል ከሆነና ሠራተኛው ወይም ወኪሉ የድርጊቱን መፈጸም የማያውቅና በተገቢው ጥረትም ሊያውቀው እንደማይችል በበደለ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ይቀጣል።

፰/ ማንም ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ(፩) የተመለከቱትን ግዴታዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተወጣ እንደሆነ አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

፱/ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈፃፀማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ እሰከ ብር ፶ ሺህ ሀምሳ ሺህ/ በማይደርስ መቀጫና እስከ ሶስት አመት በማይደርስ እስራት ይቀጣል።

shall be punishable with rigorous imprisonment from seven to ten years and with fine from Birr 50,000 to Birr 100,000, unless he can prove sufficiently to the court that he had no knowledge and could not, by the exercise of reasonable diligence, have had knowledge of the commission of the offence.

7/Where the offence is committed by an employee or an agent of a body corporate, such employee or agent shall be punishable in accordance with sub- article (6) of this Article, unless he can prove sufficiently to the court that he had no knowledge and could not, by the exercise of reasonable diligence, have had knowledge of the commission of the offence.

8/ Whosoever intentionally or negligently fails to respect fully or partially the duties provided under sub-article (1) of Article 42 of this Proclamation shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code.

9/ Any person who violates or obstructs the implementation of other provisions of this Proclamation or the Regulations or Directives issued to implement this Proclamation shall be punished with a fine up to Birr fifty thousand (50,000) and imprisonment up to three years.

፶፪. ብሔራዊ የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋት ኮሚቴ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በብሔራዊ ባንክ የሚመራ ብሔራዊ የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋት ኮሚቴ ለማቋቋም ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፶፫. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩/ በብሔራዊ ባንክ ሊቀርብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ብሔራዊ ባንክ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፶፬.ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ) አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፪ሺ፩፡

፪/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፶፯/፪ሺ፩፣

፫/የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተዳደርን እንደገና ማደራጀት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፸፪/፪ሺ፩፣

52.National Financial System Stability Committee

The Council of Ministers may issue Regulation to establish a National Financial System Stability Committee which will be chaired by the National Bank.

53.Power to Issue Regulation and Directive

1/ Based on the initiation of the National Bank, the Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The National Bank may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

54.Repealed and Inapplicable Laws

1/ The National Bank of Ethiopia Establishment (as amended) Proclamation No.591/2008.

2/ Administration of Employees of National Bank of Ethiopia Council of Ministers Regulation No.157/2008.

3/ Reorganization of the Management of the National Bank of Ethiopia Council of Ministers Regulation No. 172/2009.

፬/ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፰/፩ሺ፱፻፺፭፡

፭/ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፶፭.የማቆያ ድንጋጌ

፩/ በተሻረው አዋጅ መሠረት የወጡት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፯/፪ሺ፩ እና የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹፪/፪ሺ፲፫ ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጣጣሙ እስካልሆኑ እና ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው አዲስ መመሪያ ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

፪/በተሻረው አዋጅ መሠረት የወጡ መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጣጣሙ እስካልሆኑ ድረስ እና በአዲስ መመሪያ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

4/ The Revised Regulation on the importation of goods on Franco-Valuta basis Council of Ministers Regulation No.88/2003.

5/ No law, Regulation or Directive, inconsistent with the provisions of this Proclamation, shall have force with respect to matters provided for in this Proclamation.

55.Saving Provision

1/ Administration of Employees of National Bank of Ethiopia Council of Ministers Regulation No.157/2008 and Establishment and Operation of Ethiopian Deposit Insurance Fund Council of Ministers Regulation No.482/2021 issued in accordance with the repealed Proclamation shall continue to be effective to the extent that it is not inconsistent with this Proclamation and until such time as it is replaced by new National Bank Directive or Regulation to be issued by the Council of Ministers, respectively.

2/ Directives issued in accordance with the repealed Proclamation shall continue to be effective to the extent that they are not inconsistent with this Proclamation and until such time as they are replaced by new Directives.

፫/ በሌሎች ሕጎች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ተጠሪነታቸው ይቀጥላል፡፡

፶፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ከብሔራዊ ባንክ ለመንግስት የተሰጠው ብድር፣ ብሔራዊ ባንክ ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር በሚወስነው መሰረት መንግስት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚከፍል ይሆናል፡፡

፶፯ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

3/ Institutions that are accountable to the National Bank pursuant to other laws shall maintain their accountability

56. Transitory Provisions

Any debt owed by the Government to the National bank prior to the enactment of this Proclamation shall be settled by the Government to the National Bank as per the terms of repayment mutually agreed between the National Bank and the Ministry.

57. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 4th day of February, 2025.

TAYE ATSKE-SELASSIE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
11

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ